

# የስብከት አዘገጃጀትና አቀራረብ

ፓስተር ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ

## መግቢያ

ስብከት ማለት ምንድንው? ስብከት ማለት፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ስለተገኘው የኃጢአት ይቅርታና ደህንነት ለሰዎች የምሥራቹን ማወጅ ማለት ነው። በተጨማሪም የተለያዩ ሰዎች ስለ ስብከት ምንነት የሚከተሉትን አስተያየቶች ይሰጣሉ።

- ስብክት ማለት፥ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መልእክት ተቀብሎ ያንን የተቀበለውን መልእክት ለሰዎች ሲያስተላልፍ ነው። የእግዚአብሐርን እውነት ለሰዎች መስተላለፍና ማካፈል ነው።
- ሕይወቱ በመለኮታዊው እስትንፋስ የነቃና ህያው የሆነ አንድ ሰው እሱ ደግሞ በተራው ያንን ያገኘወን ህይወት ሰጪ መለኰታዊ እስትንፋስ ለሌላው ሲያስተላልፍና የተኛች ነፍስ እንድትነቃ ሲያደርግ ነው።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውነቶችን ለሰዎች ማስተላለፍና በባህሪያቸውና በሕይወታቸው ለውጥ እንዲታይ ማድረግ ነው።

## ሆሜሌቲክስ(Homiletics)

የስብከት አዘገጃጀትና አቀራረብ በስነ መለኮት ትምህርት "ሆሜሌቲክስ" (Homiletics) በመባል ይታወቃል። "ሆሜሌቲክስ" (Homiletics) የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የመጣው "Homilia" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ "ንግግር" ማለት ነው። ለህዝብ የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ንግግር ስበት እንዲኖረው ካስፈለገ በታላቅ ጥንቃቄና ጥበብ መዘጋጀት አለበት። ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ ሌሎችም ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን፤ የተለያዩ ስልጠናዎች ይወስዳሉ። ላቀራረባቸውም ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ሃሳብ በተሳካ ቃላትና በጥሩ አቀራረብ ሲቀርብ መንግሥትን እንኳን ሳይቀር ለማቋቋምም ሆነ ለማፍረስ እንደሚያስችል በፖለቲካው ዓለም ሲከሰት ተመልክተናል።

አንድ ሰው በሕዝብ ፊት ቆሞ የሚናገረው ነገር ካልተደመጠለት ሃሳቡም ለሰዎች የማይገባ ከሆነ የዚያ ሰው ድካም ከንቱ ነው። ንግግር ሁሉ ማስተማር፥ ማድመጥም ሁሉ መማር አይደለም። ስለዚህ ለመደመጥና ለማስተማር እንድንችል የሚያበቃና የሚጠቅም ሥልጠና መውስድ ለሚናገርና ለሚያስተምር ሰው ሁሉ አስፈላጊ ነው።

ሆሜሌቲክስ የስብከት ዝግጅትና አቀራረብን የሚያስተምር ጥበብ ነው። ጥሩ ዝግጅትና አቀራረብ ስብከትን ተደማጭነት እንዲኖረው ያደርጋል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምድር አገልግሎትም ስብከት መካከለኛ ሥፍራ የያዘ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራዎች፣ በወንዞች፣ በምኩራቦችና ዕድሉን ባገኘበት ስፍራ ሁሉ የመንግሥትን ወንጌል እንደ ሰበከ በወንጌሎች ውስጥ እንመለከታለን። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እንደተጻፈው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያገልግሎቱን ዓላማ ሲገልጽ ስብከት ባገልግሎቱ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንደያዘ ግልጽ አድርጎታል። "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን፣ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እስብክ ዘንድ ልኮኛል።" (ሉቃስ 4፡ 18-19)

በመጨረሻም ስራውን ጨርሶ ከዚህ ዓለም ሊሄድ ሲል ለደቀመዛሙርቱ ትዕዛዝ ሲሰጣቸው እንዲህ ብሏል። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።" (ማርቆስ 16፥15)እነዚህን ከመሳሰሉት ጥቅሶች መረዳት እንደምንችለው ስብከት በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መካከለኛ ቦታ እንዳለው ነው። የእግዚአብሔርን የምሥራች ወንጌል የምናውጀው በስብከት ነው። ስብከት ተራ ንግግር ሳይሆን በሰዎች ነፍስ ላይ ያተኰረ ሥራ ነው። ለምሳሌ አንድ አናጢ የሚሰራውን ሥራ በጥንቃቄ ባይሰራ የሚሰራውን ቤት ያበላሻል። ነገሩ የሚመረጥ ባይሆንም አንድ አናጢ ስራውን በጥንቃቄ ባይሰራ የሚያበለሸው የሰራውን ቤት ብቻ ነው። አናጢ ሲሰራ ያበላሸውን ቤት አፍርሶ እንደገና የመሥራት ዕድል አለው። የሰባኪ ሥራ ግን ከሰው ህይወት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ ስራውን በጥንቃቄና በማስተዋል መስራት አለበት። ሰባኪ እንደ አናጢው ያበላሸውን ለማፍረስና እንደገና ደግሞ ያንኑ መልሶ የመስራት ዕድል የለውም። ሰባኪ የሚሰራውን በትክክሉ ለመሥራት አስቀድሞ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። የስብከት አዘገጃጀትና አቀራረብ (የሆሜሊቲክስ) ትምህርትና ሥልጠና ለሰባኪዎች የሚያስፈልገውም ለዚህ ነው።

## የስብከት ዋና ግብ

ስብከት ከቤተክርስቲያን ሕይወት መላቀቅ የማይችል ዋና አሰፈላጊ ተግባር ነው። ቤተክርስቲያን ራሷ በዚህ ምድር የተመሠረተችውና መኖር የጀመረችው ሰዎች የወንጌሉን ምሥራች እያወጁ በመስበካቸው ነው። (የሐዋርያት ሥራ 2፦14-47)ዛሬም ቢሆን የቤተክርስቲያን ሕይወት የሚጠበቀው በስብከት ነው። በቤተክርስቲያን ታሪክ ሁሉ እንደተከሰተው የቤተክርስቲያን ጥንካሬና ብርታት ከፑልፒት ከሚሰበከው ስብከት ጋር ይያያዛል። ከፑልፒት የሚፈልቀው መልእክት በቃሉ እውነት ላይ የተመሠረተና የፀና ሲሆን ቤተክርስቲያን ትፀናለች፣ ትበረታለች። ከፑልፒት የሚወጣው ስብከት ደካማ ሲሆን ቤተክርስቲያንም ትደክማለች።

ሰብከት በክርስትና እምነት አስፈላጊ ቦታ አለው። የክርስትና እምነት የተጀመረው አማኞች ክርስቶስ በመሰቀል ላይ ያደረገውን ሥራና ትንሳኤውን በድፍረት በመሰበካቸው ነው። ሰብከት ዝም ብሎ የሚደረግ ተራ ንግግር ሳይሆን ዓላማ ያለው ነገር ነው። የስብከት ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ለማድረግና ለማስተዋወቅ። (ዮሐንስ 12፥32)
- ስብከቱን ሰዎች ሲሰሙ በኃጢአታቸው ተፀፅተው ወደ ንስሀ እንዲቀርቡ ለማድረግ። (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1-5) በተለይ ወንጌልን ላላመኑ ሰዎች በምንሰብክበት ጊዜ ዕድሉን ሁለተኛ ለማግኘት እንደማንችል ቆጥረን ልክ በሞት ጣር ላይ ሆኖ ጊዜ እንደሌለውና እነርሱም ለሚሞቱ ሰዎች እንደሚናገር ሰው አድርገን መስበክ ይገባናል።
- ሰዎች በክርስቶስ ደህንነትን እንዲያገኙ። (የሐዋርያት ሥራ 4፥12)
- አማኞች እንዲታነጹና እንዲያድጉ ለማድረግ።

የስብከት ግቡ ሰዎች ንስሀ እንዲገቡና እንዲለወጡ፣ የተለወጡት ደግሞ በክርስቶስ እውቀት እንዲያድጉ ስለሆነ እውነቱ በፍቅር ሊነገራቸው ያስፈልጋል። ከመድረክ ላይ የሚመነጭ ሳሙና የኃጢአተኞችን ኃጢያት አያጥብም። ሰዎች ከኃጢአት ሊነጹና ሊጠሩ የሚችሉበት መንገድ ቃሉ በትክክል ሲሰበክላቸው ብቻ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ሰባኪ በጣም ወደታወቀ አንድ የእንግሊዝ ተዋናይ (actor) ቀርቦ የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቀው "አንተ በየምሽቱ ሰው በተሰበሰበበት አዳራሽ መድረክ ትቆምና የፈጠራ ወሬና ተረት ለሕዝብ ትናገራለህ። የምትናገረውን ያደመጠ ሰው ሁሉ እንደገና ሊሰማህ ተምልሶ ይመጣል። ካንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ስትሄድም ሕዝቡ ተከትሎህ በየቦታው ይዞራል። እኔ ደግሞ ለሰዎች ሁሉ የሕይወት መዳን አስፈላጊ የሆነውን የማይለወጠውን የዘላለም እውነት በየጊዜው እሰብካለሁ። ነገር ግን ያንተን ያህል ሰው ሊሰማኝ አይሰበሰብልኝም። ባንተና በእኔ መካከል ያለው ልዩነት የፈጠረው ነገር ምንድነው?" ተዋንያኑም ሲመልስለት፥"በሁለታችን መካከል ያለው ልዩነት በጣም ግልጽና ለመለየት የማያስቸግር ነው። እኔ ልብ ወለድና የፈጠራ ወሬዬን ልክ እውነት እንደሆነ አድርጌ ለህዝቡ አቀርባለሁ። አንተ ደግሞ የምትሰብከውን እውነት ልክ እንደ ተረትና የፈጠራ ነገር አድርገህ ትሰብካለህ። በሁለታችን መካከል ያለውን ልዩነት ያመጣው ይህ ብቻ ነው" አለው። የስብከት ግቡ ከላይ የዘረዘርናቸውን ሃሳቦች ለመፈጸም ስለሆነ በቃሉ የተገለፀውን እውነት ከልባችን በፍቅርና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማስተማር አለብን።

## ሰባኪ (መልዕክተኛ)

ስብከት ማለት አንድ ሰው ለሌሎች ሰዎች የሚያስተላልፈው የእግዚአብሔር እውነት ነው። ስለሆነም ሰባኪ ባይኖር ስብከት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። እግዚአብሔር በዘላለማዊ እቅዱ ያወጣውና ያፀደቀው እቅድ ሰባኪዎች የወንጌሉን እውነት ለሰዎች እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ነው።

ሰባኪ ሰማያዊውን መልእክት ይዞ የተላከ መልእክተኛ ነው። ዋና ተግባሩ ሰዎች ቢሰሙም ባይሰሙም የእግዚአብሔርን እውነት ማወጅ ነው። (ሕዝቅኤል 2፥5፣ 3፥11) አንድ ጊዜ አንድ ሰው ጂ. ካምቤል ሞርጋን ለተባሉ ሰባኪ "ሰባኪ የጊዜውን መንፈስ የተከተለና የያዘ መሆን አለበት።" አላቸው። ካምቤል ሞርጋንም ይህንን ሲሰሙ ቶሎ ብለው፥ "ጌታ ሆይ! እንደዚህ የሚያደርገውን ሰባኪ ይቅር በለው! የሰባኪ ጥሪ የሚለዋወጠውን የጊዜውን መንፈስ ማረምና ማስተካከል ነው እንጂ የጊዜውን መንፈስ መከተል አይደለም።" ሲሉ መለሱ። አንዳንድ ሰዎች "የጊዜው ቃል" ወይም "Rehama" የሚለውን ሃሳብ ሲሰሙ ነገሩ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይሁን አይሁን ሳይፈተን ሰባኪዎች ሁሉ እንደ ዘመኑ ሰባኪዎች አንድ ዓይነት ነገር ማድረግ ወይም መናገር ያለባቸው ይመስላቸዋል። "የጊዜው ቃል" ትክክለኛ ትርጉም መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ወስዶ ሰባኪው ለሚሰብክላቸው ሰዎች አስፈላጊ የሆነ ቃል ሲሰጥና ሰባኪውም ጌታ በልቡ ያደረገውን ቃል ሲናገር ማለት ነው እንጂ በጊዜው የሚገኙትን ሰባኪዎች መምሰልና መቅዳት ማለት አይደለም። ሰባኪ እንደመልእክተኛነቱ እግዚአብሔር ከቃሉ በልቡ ያደረገውን እውነት ሳይፈራ ማቅረብ አለበት።

## ስብከት በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን ዘመን ስብከት ከእግዚአብሔር እንድሚሰጥ ይቆጠር ነበር። ኖህ "የጽድቅ ሰባኪ" ነበር። (2ኛ ጴጥሮስ 2፥5) ኖህ የእግዚአብሔር መልእክት በመስበኩና ሰዎች መልእክቱን ባለመቀበላቸው በስብከቱ ተኰነኑ (ዕብራውያን 11፥7)። ነቢያትም የእግዚአብሔርን እውነት በትንቢት መልክ ለህዝቡ ያቀረቡ የዘመኑ ሰባኪዎች ነበሩ። በባቢሎን ምርኮ ዘመንና በኋላም የምኩራቦች አገልግሎት የእግዚአብሔርን ቃል ለህዝብ ይነበብ ነበር። በእነዚህ ምኩራቦች ሁሉ ከቃሉ ለህዝብ መልእክት የሚሰጡ ሰባኪዎች ነበሩ። ጌታ ኢየሱስም በምኩራብ ተገኝቶ መልእክት (ስብከት) እንዳቀረበ (ሉቃስ 4፥17-22) ላይ እናነባለን። (የሐዋርያት ሥራ 13፥15) ላይ እንደምናየው ደግሞ ጳውሎስና በርናባስ በሰንበት ቀን አንጾክያ ባለው ምኩራብ ውስጥ ገብተው እንደተቀመጡና ሕግና ነቢያት ከተነበቡ በኋላ የምኩራቡ አለቆች ሁሉቱንም፥ "ወንድሞች ሆይ ሕዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ።" ብለው ሲጠይቋቸውና ጳውሎስም ተነስቶ እንደ ሰበከ እናያለን። ይህ ሁሉ የአይሁድ እምነት ሰባኪዎች እንደነበሩት ማስረጃ ነው። ያለሰባኪ ስብከት የለም።

## ስብከት በአዲስ ኪዳን

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሲጽፍ "የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል" ይላል። (ሮሜ 10፥13) ቀጥሎም ሰዎች "ያላመኑትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል?" የሚል ጥያቄ በማቅረብ ሰዎች የሚድኑት የእግዚአብሔርን ስም ዝም ብሎ በመጥራት ሳይሆን አምነው ሲጠሩት እንደሆነ ካሰረገጠ በኋላ (ሮሜ 10፥14) "ካልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?" በማለት ሰባኪ ከሌለ ስብከት እንደሌለና ፣ ሰዎች ደግሞ ስብከት ሳይሰሙ መዳን እንደማይችሉ አስገንዝቧል። በተጨማሪም ሃዋርያው ከኢሳያስ 52 "መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው?" የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ የሰባኪንና የስብከትን አስፈላጊነት ጠቁሟል። (ሮሜ 10፥15) ያለሰባኪ ሰዎች መልካሙን የምሥራች ሊሰሙ የሚችሉበት መንገድ የለም። እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ያቀደው ሰዎች (ሰባኪዎች) የወንጌሉን የምሥራችና የቃሉን እውነት እንዲያወጁ ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 1፥21)

ስለዚህ ሰባኪ የእግዚአብሔር እውነት ማስተላለፊያ መሣሪያ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ መልእክቱ ለሰዎች እንዲደርስ ስለሆነ ሰባኪ ጥሩ የመልእክት ማስተላለፊያ ሆኖ መቅረብ አለበት። ደግሞም በውስጡ ማለፍ የሚገባው መልእክት ለሰዎች ከመተላለፍ እንዳይታገድ ወይም ጥራቱ እንዳይበላሽ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል።

የሰባኪ ሥራ ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ አንድ ሰው ከመድረክ ቆሞ ከመሰብኩ በፊት ሊኖረው የሚገባው ብዙ አስፈላጊ ነገሮች አሉ። ከስብከት በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች፥

- የደህንነት ልምምድ፥ ሰብከት ከአለማዊው ወይም ከተራው ንግግር (ዲስኩር) የተለየ ነገር ነው። አንድ ሰው በግል ኢየሱስ ክርስቶስን ሳያውቅና ሳይድን ስለማያውቀው ሕይወትና ጌታ መናገር አይችልም። መናገርም የለበትም። ሳይድኑ በፊት ሌሎችን በማዳን ሥራ ላይ መሰለፍ ፈጽሞ አይቻልም። ሌሎችን "ኑ" ብሎ መጥራት የሚችል ራሱ የሚሄድበትን ያወቀ ብቻ ነው።
- ሰማያዊ ጥሪና የመስበክ ፀጋ፥ አማኝ ሁሉ ለመመስከር ተጠርተዋል። ደግሞም ካማኞች መካከል አንዳንቹ ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠትም ሆነ ሳይሰጡ ወንጌልን እንዲሰብኩ ከእግዚአብሔር የመስበክ ፀጋ የተሰጣቸውና የተቀቡ አሉ። ስለዚህ ሰባኪ ለመሆን ጥሪና የመስበክ ፀጋ አስፈላጊ ነው።
- የነፍሳት ፍቅር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች የሰበከው ለነፍሳት ፍቅርና ርኅራኄ ስለነበረው ነው። ለሚጠፋት ያለቀሰውና በመጨረሻም ደሙን ያፈሰሰው ከፍቅሩና ከርኅራኄው የተነሳ ነው።። የወንጌል ሰባኪም የዚህ ዓይነት ቀስቃሽ ዓላማና ምክንያት ሊኖረው ይገባል። ከዚህ ከተለየ መነሻ ምክንያት ተነስቶ ሰባኪ መሆን ይቻላል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ወንጌልን ለተለየ ዓለማ የሰበኩ ሰዎች እንዳሉ ተጽፏል። (ፊልጵስዮስ 1፥15-18) ነገር ግን እውነተኛ ሰባኪ እንዲሰብክ የሚገፋፋው ቀስቃሽ ምክንያቱ የነፍሳት ፍቅርና ርኅራኄ ብቻ ነው።
- በመንፈስ ቅዱስ መታመን፥ ሰባኪ የሚናገራቸው ነገሮች ሁሉ የሰውን ልብ የሚነኩትና የሚለውጡት መንፈስ ቅዱስ የእነኛን ሰዎች ሕይወት ሲነካ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ካልነካቸው በቀር ሰዎች ልባቸው ሊነካና ተፀፅተው ንስሃ ሊገቡ

 © 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas 

አይችሉም። ሰዎች ተፀፅተው ንስሃ በመግባት ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሚሰጡት በመንፈስ ቅዱስ ሲነኩ ብቻ ነው። ስለዚህ ሰባኪ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ከፈለገ በመንፈስ ቅዱስ መታመን ይገባዋል። (ዘካርያስ 4፥6) ገና ከዝግጅቱ ጀምሮ ከመድረክ ላይ ቆሞ በሚሰብክበት ጊዜ ሁሉ ሰባኪን የሚረዳውና የሚያግዘው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ሰባኪ የሚሰብከውን ሲያዘጋጅም ሆነ ያዘጋጀውን ለህዝብ ሲያቀርብ በመንፈስ ቅዱስ መታመን አለበት።

■ መንፈሳዊ ዲሲፕሊን፥ ሰባኪ በመጀመሪያ ለግል ሕይወቱ እድገት ቀጥሎም ለአገልግሎቱ የሚረዳ ጥሩ መንፈሳዊ ዲሲፕሊን ሊኖረው ይገባል። ከእነዚህ ዲሲፕሊኖች መካከል ሁሉንም ሳይሆን ሁለቱን ብቻ ብንጥቀስ፥

■ የሚማር መሆን አለበት። ሰባኪ መስጠት የሚችለው የተቀበለውን ያህል ነው። የማይቀበል ያለውን ሰጥቶ ሲጨርስ ያልቅበታል። ልጆች ሆነን አንዳንድ ክርስቲያኖች ቃሉን በግል ሕይወታቸው ሳያጡኑ "አፍህን ክፈት እኔም እሞላዋለሁ።" ተብሏል በማለት የግል ሕይወታቸውን እድገት ሆነ አልግሎታቸውንም ሲጎዱ ታይተዋል። ሰባኪ ለመስበክ በተጋበዘ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ቃል በየጊዜው ማጥናት አለበት። ይህን ማድረግ ለግል ሕይወቱ እድገት ይጠቅመዋል፤ በተጨማሪም በሚያገለግልበት ጊዜ ከቃሉ ያገኘውን ዕውቀት ለማካፈል ይረዳዋል። የሰው መንፈስ ማደግና መዳበር እንዳለበት አዕምሮም እንዲሁ ማደግ አለበት። ስለ እግዚአብሔር ቃል ያለን ዕውቀት መስፋትና መዳበር የሚገባው ለዚህ ነው።

■ የሚፀልይ መሆን አለበት። ሰባኪ በግል ሕይወቱ ጥሩ የፀሎት ዲሲፕሊን ሊኖረው ይገባል። ሰባኪ የሚፀልየው የሰበከ ቀን ወይም ቀደም ብሎ ከሰብከቱ ጋር ለተያያዘ ነገር ብቻ መሆን የለበትም። ጸሎት ክርስቲያን መንፈሳዊ ህይወቱን ሊያዳብርበት ከሚችልበት አምስት ዲሲፕሊኖች አንዱ ነው። ሰባኪ በግል የፀሎት ሕይወቱ የጠነከረ መሆን አለበት። የግል ሕይወቱ የፀሎት ዲሲፕሊን ከሌለው ለሚሰጠው አገልግሎትም በትክክሉ መፀለይ አይችልም። ሰባኪ በመድረክ ላይ የሚሰማው ብዙ ኃይል ለብዙ ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ ከእግዚአብሔር የመነጋገሩ ውጤት ነው።

■ ሰባኪ ሌላውን ሰው የሚኮርጅ (imitator) መሆን የለበትም፥ አንዳንድ ሰባኪዎች ያዩትንና የሚያደንቁትን ሰባኪ የመምሰል ፈተና አለባቸው። ሰባኪ እንደማንኛውም ሰው ያወቀውን ነገር ለማቅረብ የግድ ሌላውን ሰው መምሰልና ያንን ሰው ሙሉ በሙሉ መቅዳት (ኮፒ ማድረግ) አያስፈልገውም። ሊሆን የሚገበው ራሱን ነው። ያወቀውን እውነት በራሱ ሰብእና (personality) ለማቅረብና ለመግለጽ መቻል አለበት። በምድር ላይ እግዚአብሔር አንዱ የሌላው ሙሉ ቅጂ (አንድ ዓይነት )እንዲሆኑ አድርጎ ሁለት ሰዎች የሉም። እያንዳንዱ ሰው ልዩ ነው። ዳዊትን ከሆኑ የሳዖልን የጦር ልብስና ትጥቅ ታጥቆ ጦር ሜዳ መሄድ አያስፈልገም። የእረኛ ትጥቅ ታጥቆ መውጣትና በእግዚአብሔር እርዳታ ወንጭፍን ብቻ መወንጨፍ ተገቢ ነው። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ሌላውን ለመሆን ሲሞክር ሥራው ፍሬ ቢስ ይሆናል። የሚሰሙን ሰዎች ደግሞ ሌላውን እንደምንቀዳ ካወቁ ሊያዳምጡን ያላቸው ፍላጐት ይጠፋል። በተጨማሪም ሌሎችን የሚቀዱና የሚኮርጁ ሰዎች የሚቀዱትና የሚኮርጁት የእነኛን ሰዎች ስህተት ጭምር ስለሆነ የቀዷቸው ሰዎች የሚሠሩትን ስህተት እነርሱም ይፈጽማሉ።

■ ሰባኪ ሕይወቱን መጠበቅ አለበት። አገልግሎት ሕይወት ነው። የምንናገረውን በምንኖረው ሕይወት ካልደገፍነው ሰዎች አገልግሎታችንን መቀበል ይከብዳቸዋል። ከምንናገረው ቃል ይልቅ ማንነታችን በሰዎች ጆሮ ላይ የበለጠ ይጮሃል። እንደ ስብከታችን የማንኖር ከሆነ ሰዎች ቀስ በቀስ ያንን ማወቃቸው አይቀርም። ሃዋርያው ጳውሎስ ደጋግሞ ወጣት የነበረውን ሰባኪ ጢሞቴዎስን ስለንጽህና እና የሕይወት ቅድስና የጻፈለት ለዚህ ነው። ስለዚህ ሰባኪ የግል ሕይወቱን መጠበቅ አለበት። ሌላው ቀርቶ አንድ ሰባኪ በስብከቱ ጊዜ በውሸት እግዚአብሔርን ለማክበር ከመሞከር እንኳን የሚጠነቀቅ ሊሆን ይገባዋል። ከፑልፒት ላይ ነገርን ማጋነን፣ (exaggeration) ወይም ውሸትን መናገር ከመድረክ ውጭ ሊደረጉ ከሚችሉት ኃጢአቶች ይልቅ የከፋ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስም ውሸት መናገር ነው። እግዚአብሔር ፈጽሞ በውሸት አይከብርም። ስለዚህ ይህን የመሰለ ስህተት ውስጥ እንዳንገባ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

■ ጥሩ የመድረክ ላይ አቀራረብ። በመድረክ ላይ የሚቆም ሰባኪ ወክሎ የሚቆመው እግዚአብሔርን ነው። ስለሆነም ሰባኪ የሚከተሉትን ነገሮች ማሟላት ይገባዋል።

■ ጥሩ አለባበስና ንጽህና፥ በመድረክ ቆሞ የሚናገር ሰው የሰው ሁሉ አይን ያርፍበታል። ስለሆነም አለባበሱ፣ ፀጉር አበጣጠሩ፣ ንጽህናው ጥሩ መሆን አለበት። አለባበሱን፣ ፀጉር አበጣጠሩን፣ ንጽህናውን፣ በትክክል ያልጠበቀ ሰባኪ የሰዎች ሃሳብ እዚያ ላይ እንዲያተኩር ስለሚያደርግ መልእክቱን እንዳይሰሙ ያደርጋል። ስለዚህ ወደ መድረክ ስንወጣ ጥሩ አቀራረብ ሊኖረን ይገባል።

■ የድምፅ አጠቃቀሙን የሰውነት እንቅስቃሴውን ዘዴ ሊያውቅ ይገባል። ሰብከት በምናዘጋጅበት ጊዜ ለዝግጅታችን የሚረዱን ዋና ዋና ነገሮች፤

■ መጽሐፍ ቅዱስ። በክርስትና እምነት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ቦታና አስፈላጊነት የታወቀ ስለሆነ እዚህ ቦታ መጥቀሱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ሃሳብ ሁሉ የገለፀበት መጽሐፍ ነው። ስብከት የእግዚአብሔርን እውነት ማወጅና ማስታወቅ ስለሆነ ያንድ ሰባኪ የሃሳቡ ሁሉ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ መሆን አለበት።

■ የሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት። አንድ ሰባኪ ስብከት ለማዘጋጀት መጽሐፍ ቅዱሱን ማንበብ ማጥናትና ማወቅ አለበት። እንዲህ በምንልበት ጊዜ የስብከት አዘጋጃጀት በሚለው ርዕስ ስር ወደፊት እንደምናየው የመሰበክ እድል ሲያጋጥመው ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያገላብጥ ማለት ሳይሆን፥ በግል ህይወቱ እንደ ክርስቲያንነቱ ሊኖረው ስለሚገባው ዲሲፕሊን መጥቀሳችን ነው። ስለ የግል ጸሎት አስፈላጊነት ስንጠቅስ እንዳልነው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማጥናት

ማንኛውም አማኝ ሊኖረው ከሚገባው አምስት ዲሲፕሊኖች መካከል አንዱ ነው። ሰባኪ መጽሐፍ ቅዱሱን ያላነበበና ያላወቀ ከሆነ መስበክ (መናገር) ባያቅተውም መልእክት የለውም። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ያልተመሠረተ ስብከት ተራ ንግግር እንጂ ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው ብዙ የክርስትና ልምምድ ቢያካብት እንኳ፣ ቃሉን ካላወቀ ሰዎችን ሳያሳስት ልምምዱን ለሌሎች ማቅረብ አይችልም። እንዲያውም ሌላውን ሳያሳስት ልምምዱን ለማቅረብ ቀርቶ ለራሱም እንኳ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አይችልም። ከቃሉ ያልወጣና በቃሉ ያልተደገፈ ልምምድ ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት አይደለም። ስለዚህ ለመስበክ የሰባኪው የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ የግድ አስፈላጊ ነው።

■ ሰባኪው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው አመለካከት፥ ሰባኪው መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ስህተት የማይገኝበት ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉት እንደሆነ እንዲሁም በእምነት ጉዳዮች የመጨረሻው ባለሥልጣን እንደሆነ ማመን አለበት። ሰባኪው የዚህ ዓይነት አመለካከትና አክብሮት ለቃሉ ሳይኖረው፥ ሌሎች የቃሉን ሃሳብ በአክብሮት ተቀብለው ለሕይወታቸው መመሪያ አደርገው እንዲጠቀሙበት ማድረግ አይችልም።

■ የሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች በግል ሕይወቱ መለማመድ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ማንኛውም መጽሐፍ ለዕውቀት ብቻ የሚያነቡትና በቃል የሚደጋግሙት መጽሐፍ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ የምናነባቸውን እውነቶች በግል ሕይወታችን ልንለማመዳቸው ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንድ ሰው ከመዝሙር 23 “እግዚአብሔር እረኛዬ ነው።” የሚለውን ቃል በማንበብ ማወቅ ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔርን በእርግጥ የነፍሱ እረኛ ከላደረገው ይህንን ቃል ማወቁና መናገሩ ብቻ ሰባኪ አያደርገውም። በአገራችን የታወቀ አንድ አፈ ታሪክ አለ። የሰንበት ቀን ቄሱ ለሰዎች “መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ያለው አንዱን ይስጥ።” ይላል እያሉ ያስተምራሉ። ሰውዬው ይህንን ሲያስተምሩ ሚስታቸው በዚያ ቦታ ስለነበሩ ይህን ሰምተው ቤታቸው በሚሄዱበት ጊዜ አንድ ያረጀና የተቀዳደደ ልብስ የለበሰ ለማኝ ከበራቸው ቆሞ ሲለምን ያያሉ። እርሳቸውም የባላቸው (የቄሱ) ትምህርት ትዝ ይላቸውና ወደ ጓዳ ገብተው የቄሱን ልብስ አውጥተው ለለማኙ ይሰጣሉ። ቄሱ ወደ ቤት በሚመጡና የሆነውንም በሚያውቁበት ጊዜ ይቆጣሉ። ሚስትየውም፥ “እንዴ! እርስዎ ሁለት ያለው አንዱን መስጠት አለበት ተብሎ ተጽፏል ሲሉ ያስተምሩ አልነበረምን?” ይሏቸዋል። እርሳቸውም ሲመልሱ፥ “ታዲያ እኔ እንዲያ ያልኩት ለሌሎች እንጂ ለእኛ ነው እንዴ?” ሲሉ መለሱ ይባላል። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በግል ሕይወት ሳይለማመዱ ለሌሎች መስበክ ከዚህ ከቄሱ ታሪክ የተለየ አይደለም።

ሰባኪ የሚናገረው እግዚአብሔርን ወክሎ ከሆነ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከገለጸበት ቃሉ ጋር የጠበቀ ትውውቅ ያስፈልገዋል። በስብከት የሚቀርበው መልእክት ሁሉ ሰባኪው አዲስ የሚፈጥረው ሃሳብ ሳይሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ የገለፀውና በቃሉ የጻፈው መሆን አለበት። ሰባኪ ሊናገረው የሚገባው ሃሳብ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ። ከሰባኪ የሚጠበቀው ቃሉን ማንበብ፣ በትክክሉ መተርጐምና፣ በተግባር ማዋል፣ ከዚያም ለሌሎች ማስረዳት ነው። ስለዚህ ነው ለስብከት ከሁሉ ነገር መጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት አስፈላጊ የሚሆነው።

■ በሥርዓት ተዘጋጅቶ የተጻፈ ትምህርተ መለኰት (Systematic Theology)። እንደ ቤተ እምነቱ የቤተ እምነቱ አስተምህሮና አመለካከት የተንፀባረቀባቸው ልዩ ልዩ የትምህርተ መለኰት መጽሐፎች አሉ። ትክክለኛውን እውነት ለማስተማር ብሎም በቂ እውቀት እንዲኖርና ለስብከት ዝግጅት እንዲረዳን እነዚህን መጽሐፎች ማንበብ አስፈላጊ ነው። ለዕውቀት ያህል ሁሉንም ዓይነት ጽሑፎች ማንበብ ጠቃሚ ቢሆንም፥ እኛ አባል የሆንንበት ቤተ እምነት ትክክለኛ አስተምህሮ ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ጴንጤ ከሆኑ የጴንጤ ቤተ እምነት አስተምህሮ (ዶክትሪንስ)ምን እንደሆነ ማወቁ አስፈላጊ ነው።

■ መንፈሳዊ መጽሐፎች፥ በተለያዩ አማኞች የተጻፉ ብዙ መንፈሳዊ መጽሐፎች አሉ። መንፈሳዊ እውቀታችንን ለማዳበር እነዚህን መጽሐፎች ማንበብ ለግል መንፈሳዊ ሕይወታችንና ዕውቀታችን ከመርዳቱም በላይ ለስብከት ዝግጅታችን ይረዳል።

■ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እውቀት። የቀደሙትን ክርስቲያኖች ታሪክ በየዘመናቱ ቤተ ክርስቲያን ያለፈችባቸውን ሁኔታዎች፤ በጊዜው የነበረውን ባህልና ሁኔታ ማወቅ ለማንኛውም አማኝ በተለይም ለሰባኪዎች አስፈላጊ ነው። (ማቴዎስ 25) ላይ ያለውን የአሥሩን ቆንጃጅት ታሪክ እንደ ምሳሌ ብንመለከት ሙሽራው የሚመጣው በሌሊት እንደ ሆነ እናያለን። ለምን የሙሽራው መምጫ በሌሊት ሆነ? የዚህን ምክንያት ከሌሎች ባህሎች ተነስቶ መረዳትና ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም በብዙ ባህሎች ሙሽራው ሙሽሪትን ለመውሰድ ወደ ቤቷ የሚመጣው በቀን ነው። ሙሽራው በሌሊት የመጣበትን ምክንያት ለማወቅ የግድ በጊዜው በእሥራኤል የነበረውን የሠርግ ባህል ማወቅ ያስፈልጋል። እንደዚሁም (ዮሐንስ 21፥ 7) ላይ ጴጥሮስ ራቁቱን ስለነበር ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ መምጣቱን ሲሰማ ራሱን ወደ ባህሩ እንደ ጣለ እናነባለን። ይህ ምን ማለት ነው? ጴጥሮስ ለምን ይህን አደረገ? እዚህ ላይ ጴጥሮስ ዕርቃነ ሥጋውን ነበር፣ በላዩም ምንም ጨርቅ አልነበረም ማለት ነው? ወይስ ሌላ ትርጉም አለው? ትክክለኛውን ነገር ማወቅ የሚቻለው በዘመኑ የነበረውን ባህልና የአነጋገር ዘይቤ ስንረዳ ነው። ጴጥሮስ ለሥራ ትንሽ ጨርቅ አገልድሞ ለብሶ ነበር እንጂ እርቃነ ሥጋውን አልነበረም። ተመሳሳይ አባባል እኛም አገር አለ። እናቶች በውስጥ ልብስ ብቻ ሆነው ሰው ቢመጣባቸው ይህንኑ አባባል ይጠቀሙበታል። ይህንን የመሰሉትን ሃሳቦች የምንረዳው ከታሪክ፥ በጊዜው ከነበረው ባህልና ልማድ፥ ... ወዘተ ነው።

■ ልዩ ልዩ ሰባኪዎች የሰበኩት ስብከቶች፥ እነዚህን ስብከቶች የምናነበው እንዳለ ገልብጠን ለመስበክ ሳይሆን በምንሰብክበት ርዕስ የታወቁና እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሌሎች አገልጋዮች ምን እንዳሉ ለማወቅ ነው። ከእነዚህ ስብከቶች

አንዳንድ ሃሳቦችን ወስደን በስብከታችን ልንጠቀባቸው እንችላለን፡፡ የሌሎችን ሰዎች ስብከት ከየት እንዳገኙት ሳይገልጹ እንዳለ ሙሉ በሙሉ ገልብጦ መስበክ ትክክል አይደለም፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ወደ አንድ ቤተክርስቲያን ሄዶ አንድ ስብከት ይሰብካል፡፡ ስብከቱን የሰሙት ሁሉ በስብከቱ ልባቸው እንደ ተነካ ይገልጹለታል፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ ሌላ ቦታ ደግሞ ይጋበዛል፡፡ እርሱም ያንን ከዚህ በፊት የብዙ ሰዎችን ልብ የነካ ስብከቱን ለመስበክ ወስኖ ሄደና ሰበከ፡፡ በዚያ ቤተክርስቲያን ስብከቱን የሰሙት ግን እንደ መጀመሪያው ቤተክርስቲያን ሰዎች በስብከቱ ምንም ዓይነት መደነቅና መነካት አላሳዩም፡፡ እርሱም ነገሩ አስገርሞት ፓስተሩን "ለምንድነው ሰዎች በስብከቴ ብዙ ያልተነኩት?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ፓስተሩም ከሁለት ሳምንት በፊት አንድ ሰው ከሌላ ቤተክርስቲያን መጥቶ ይህንኑ ስበከት እንዳለ ቃል በቃል ስብኮት ስለነበረ ነው፡፡" ሲል ይመልስለታል፡፡ ለካስ ሰባኪው መጀመሪያ ከሰበክበት ቤተ ክርስቲያን ስብከቱን የሰማ አንድ ሰው ወደዚህ መጥቶ ስብከቱን እንዳለ ቃል በቃል ሰብኮታል፡፡ ከሰማነውና ካነበብነው ስብከት የተመጠነ ሃሳብ መጠቀም መልካም ነው፡፡ እንዳለ መገልበጥ ግን ከላይ ያለውን ዓይነት ችግር ከመፍጠሩም ሌላ በስብከቱ በሚገኘው ፍሬ ዋጋ የሚቀበለው በመጀመሪያ ያንን ስብከት ለፍቶ ያዘጋጀው ሰው ነው፡፡ እርግጥ ነው በመስበካችን ብቻ ዋጋ ብናገኝም የምንቀበለው ዋጋ ስብከቱን በጉልበቱ ተንበርክኮ በመጸለይ ተቀብሎ እንደ ሰበከው ሰው እኩል አይሆንም፡፡

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ቃል በሥራ ላይ የዋለበትን የተለያዩ ስፍራዎች የሚመራ መጽሐፍ። (concordance)
- የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳቦችን በተመለከተ የተዘጋጁ የሊቃውንት አስተያቶች። (Commentaries)
- መዝገበ ቃላት (Dictionary)

በስብከት አዘገጃጀት ጊዜ ሰባኪ ብዙ ጥንቃቄዎች ማድረግ ይጠበቅበታል። በቅድሚያ ይህንን ስብከት የምሰብከው ለምን ዓይነት አድማጮች (audience) ነው? ብሎ መጠየቅና መልሱን ማግኘት አለበት፡፡ የኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው? የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው? ያገቡ ሰዎች ስብሰባ ነው? ያላገቡ (singles) ሰዎች ስበሰባ ነው? የከተማ ሰዎች ናቸው? ወይስ የገጠር ሰዎች ናቸው? እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችም ጥያቄዎች ጠይቆ መልሱን ማግኘት ለስብከት አዘገጃጀት ይረዳል፡፡ ዋናው የወንጌል መልእክትና የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል (መልእክቱ) ምንጊዜም አይለወጥም፡፡ ለተለያዩ ሰዎች መልእክቱን የምናቀርብበት መንገድ (method) እና አቀራረብ ግን እንደ አድማጮቹ ማንነት ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ አድማጮቹ ሁኔታ የመልእክቱን አቀራረብ እንደ ለወጠ ብዙ ሰዎች ይስማማሉ፡፡ (የሐዋርያት ሥራ 13፣ የሐዋርያት ሥራ 17፣ የሐዋርያት ሥራ 20 ይመልከቱ) ለምሳሌ ከግሪክ ፈላስፎች ጋር በተነጋገረ ጊዜ እነርሱ ከሚያውቁት እውቀት በመጥቀስ መልእክት አቅርቧል፡፡ (የሐዋርያት ሥራ 17፥ 18-32)በተለይ ቁጥር 28 ላይ የጠቀሳቸው ባለቅኔዎች እነማን እንደነበሩ ከጥቀሱ ሃሳብ ስለሚታወቅ ጳውሎስ መጻሕፍትን ያነበበና የፈላስፎችን አዕምሮ ከሚያውቁት እውቀት ጠቅሶ መድረስ እንደሚችል ያሳያል፡፡ ስለዚህ ሁለት ዓይነት ጉባዔዎች አንድ አይነት መሆን ስለማይችሉ የአድማጮችን ማንነት ማወቅ ለመልእክት ዝግጅትና አቀራረብ ጠቃሚ ነው፡፡

ሰባኪ ከዚህ በታቸ የተዘረዘሩት ችግሮች እንዳያጋጥሙት መጠንቀቅ አለበት፤

- ከአድማጮች አእምሮ በላይ መስበክ። አንዳንድ ሰባኪዎች የአድማጮቻቸውን የዕውቀት ደረጃ ካለማወቅ የተነሳ የሚያቀርቡት ስብከቶች ከአድማጮቹ አእምሮ በላይ ስለሚሆኑ መልእክቱ ለተቀባዮቹ አይደርስም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ወደ ምድር ሥጋ ለብሶ በመጣ ጊዜ ያስተማረው ለሰዎች በሚገባ ሃሳብ፣ በሚያውቁት ምሳሌና ሊረዱት በሚችሉት አቀራረብ ነበር፡፡ በሰማይ የነበረ አምላክ በመሆኑ በዕውቀቱ ልክ ቢናገር ኖሮ ብዙ ሰዎች ትምህርቱ ይከብዳቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ሰባኪ ካድማጮቹ አዕምሮ በላይ እንዳይሰብክ ሊጠነቀቅ ይገባዋል፡፡
- ካድማጮች አእምሮ በታች መስበክ። በአእምሮአቸው ለበለፀጉ ሰዎች ያለመጠን ዝቅ ያለ ሃሳብ ማቅረብ የመልእክቱን ተደማጭነት ይቀንሳል፡፡ ለምሳሌ ለዩኒቨርስቲ ክርስቲያኖች የሰንበትን ሕፃናት እንደምናስተምር" ያዕቆብ 12 ልጆች ነበሩት … እያልን ስዕል በመለጠፍና በማሳየት ብናስተምር ትምህርቱ ከደረጃቸው በጣም ዝቅ ያለ ይሆንባቸዋል፡፡ እንዲህ ያለ ችግር እንዳይፈጠር የአድማጮችን ማንነት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
- ቃል ብቻ የሆነውን ሃሳብ አድማጮች እንዲይዙ ማድረግ፥ ክርስትና ልዩ ልዩ ክርስቲያናዊ ቃላቶችን ማወቅና ማስተጋባት ሳይሆን በልምምድ የሚገለጽ ሕይወት ነው፡፡ አንድ ሰው የምናስተምረውን ትምህርት መማር የሚችለው ሲለማመደው ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርታችን ሰዎች የቃሉን እውቀት ተቀብለው እንዲለማመዱት የሚያደርግ በመሆን ፈንታ የተወሰነ ቃል ብቻ አውቀው ያንን እንደመፈክር ሲደጋግሙ እንዲከርሙ የሚገፋፋ ከሆነ ልክ አይደለም፡፡ ስለዚህ ሰባኪዎች የሚያስተምሩትን ሁሉ በልምምድ የሚተረጐም እንዲሆን አድረገው ማስተማር አለባቸው፡፡ ነገር ግን ትምህርታቸው ሰዎችን በስሜት ብቻ አስክሮ ስለማያውቁትና ስላልተለማመዱት ነገር ቃላት እየተቀባበሉ ወርቃማ ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ የሚያደርግ ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው፡፡

## የስብከት ዓይነቶች፥

ብዙ ዓይነት የስብከት ዓይነቶች አሉ፡፡ እነርሱንም በተለያየ መንገድ መከፋፈልና ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ (The Textual Sermon, the topical sermon, the textual - topical sermon, the typical sermon, the expository sermon, the theological/doctrinal/sermon, the ethical

sermon, the biographical sermon etc.) ነገር ግን በዚህ ትምህርት የምንመለከተው ሦስት የስብከት ዓይነቶችን ብቻ ይሆናል። እነርሱም

- ሙሉ የጥቅስ ሃሳብ ላይ ያተኮረ (Textual)
- ርዕሳዊ (topical)
- ማብራራትና መተንተን ላይ ያተኮረ (Expository)

ሙሉ የጥቅስ ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ስብከት ( textual sermon) የምንለው የስብከት ዓይነት የትምህርቱ ዋና ሃሳብ (subject) እና የስብከቱ ዋና ዋና ክፍሎች ሃሳብ የሚወጣው ስብከቱ ከተመሠረተበት ጥቅስ ሲሆን ነው። ጥቅሱ አጠር ያለ (አንድ ቁጥር) ወይም ብዙ (ሁለትና ሦስት ቁጥር) ሊሆን ይችላል። የስብከቱ ዋና ሃሳብ የሚመነጨውና ተዋቅሮ በተለያዩ ንዑስ ክፍሎች ተመድቦ የሚቀርበው በዚሁ ጥቅስ ሃሳብ ላይ ብቻ ነው። ከዚህ በታች ሙሉ የጥቅስ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ (textual) ስብከት ምን እንደሚመስል አንድ ጥቅስ ወስደን ለዚያ አስተዋጽኦ (outline) በማውጣት እንመለከታለን።

## መነሻ ሃሳብ text ኢሳይያስ 40፥ 28-31 ርዕስ - የእግዚአብሔር ኃይል ለደካከሙት

ሀ) የእኛ አምላክ የሚመስለው 40፦ 28 ፈጽሞ ተሰፋ አይቆርጥም አይደክምም አይታክትም ማስተዋሉም አይመረመርም (ፈጽሞ ጥበብ አይጐድለውም)

ለ) የእኛ አምላክ የሚሰጠው 40፥ 29፣ 30 ለደካማ ኃይልን ይሰጣል ጉልበት ለሌለው ብርታትን ይጨምራል ሐ) የእኛ አምላክ ሊያደርግልን የሚፈልገው 40፥31 እንደ ንስር ከፕሮብሌሞቻችን በላይ ከፍ ለማለት የምንችልበትን ኃይል ይሰጠናል ሳይደክመን እንድንሮጥ ያስችለናል ሳንታክት እንድንራመድ (እንድንጓዝ) ያደርገናል።

## ስብከትን በጥቅስ ሙሉ ሃሳብ ላይ መመስረት ያለው ጥቅም (The Advantages of Textual Sermon)

ሀ) የሰባኪው ሃሳብ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ (Bibilical) እንዲሆን ይረዳል። ሰባኪው የጥቅሱን ሃሳብና ትርጉም ተከትሎ ከሄደ ትምህርቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ እንዳይወጣ ይጠብቃል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ከምንጊዜውም ይልቅ ትምህርታቸው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ መሠረት የሆኑ ሰባኪያን የሚያስፈልጉበት ዘመን ቢኖር አሁን ያለንበት ዘመን ነው። ብዙ ዓይነት ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ሃሳብና የተለያዩ የስህተት ትምህርቶች የሚገኙበት ዘመን ስለሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰባኪዎች ከምንጊዜውም ይልቅ በበዛት ያስፈልጉናል።

ለ) ጥቅሱ በጥንቃቄ የተመረጠ ሲሆን ያድማጮችን የመከታተል ፍላጐት ይጨምራል።

ሐ) አድማጮች ትምህርቱ የተሰጠበትን ጥቅስ ባዩ ቁጥር የሰሙትን ስብከት እንዲያስታውሱና እንዲያሰላስሉ ያደርጋል። ብዙ ሰዎች ከዚህ በፊት ስብከት የሰሙባቸውን ጥቅሶች ሲያዩ የሰሙትን ስብከት ያስታውሳሉ።

መ) በ text ላይ የተመሠረተ ስብከት - ብዙ ጊዜ መንደርደሪያው ሃሳብ (context) የት ቦታ እንደሆነ ለመፈለግ ሲባል ምዕራፎችን፣ ታሪኮችን፣ ለማንበብና ለማብራራት ዕድል ይሰጣል።

ሠ) የሰባኪው ሃሳብ ወዲያና ወዲህ እንዳይዋዥቅ ይረዳል። አንዳንድ ሰባኪዎች ወደ ውሃ ዘለው ተወርውረው ሰምጠው እንደሚሄዱ ዋናተኞች (divers) ከቃሉ ዘለው ወደሌላ ነገር ጥልቅ ጥልቅ ይሉና ይጠፋሉ። ከጠፉበት ብቅ ሲሉ የሚታዩት "አሜን" የሚለው የመጨረሻ ቃል ላይ ነው። Textual የስብከት አቀራረብ ከዚህ ዓይነት መዋዠቅና መጥፋት ሰባኪውን ለመጠበቅ ይረዳል።

ረ) ሰባኪው ያለፍርሃት በነፃነትና በድፍረት እንዲሰብክ ያስችላል። በጥቅሶቹ የቀረቡት ሃሳቦች የሰው ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆኑ ያለምንም ፍርሀት በነፃነት በቃሉ የተገለፀውን ሃሰብ በሥልጣን ለማወጅ ያስችላል።

## የ text አመራረጥ መመሪያ

የሚከተሉት ሃሳቦች ስብከት የሚመሠረትበትን ጥቅስ (text) ለመምረጥ በምንፈልግበት ጊዜ መመሪያ እንዲሆኑ የቀረቡ ናቸው።

ሀ) የማያቋርጥ የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ጥናት። አንድ ሰባኪ መጽሐፍ ቅዱሱን የሚያነበው ለመሰበክ በተፈለገበትና በተጋበዘበት ጊዜ ብቻ መሆን የለበትም። እያንዳንዱ ሰባኪ እንደ ክርስቲያንነቱ በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማወቅ አለበት። ሰባኪ ሊሰብከው የሚገባው እውነት ሁሉ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ለስብከት የሚሆን ጥሩ ጥቅስ (text) ለመምረጥ ቃሉን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ለ) ማስታወሻ መያዝ። መጽሐፍ ቅዱስ ስናነብ የምናገኘውን ሃሳብ ወይም ልባችንን የነካንን ሃሳብ በማስታወሻ መጻፍ። ልቡ የተነካበትን ጥቅስና የተማረውን ትምህርት በማስታወሻ የሚጽፍ ሰው በጥቅስ ሙሉ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ስብከት (textual sermon) ለማዘጋጀት በፈለገ ጊዜ ለስብከት የሚሆን ጥቅስ (text )ካላገኘ ቶሎ ብሎ በየጊዜው የተማረውን ወደጻፈበት ማስታወሻ ደብተሩ ሄዶ በመመልከት ለዝግጅቱ የሚሆን ሃሳብና ጥቅስ (text) ማግኘት ይችላል። እንደዚሁም በየጊዜው ሌሎች ሲያስተምሩ የምንማረውን ሃሳብ በማስታወሻ መያዝ ለስብከት ዝግጅት ይረዳል።

ሐ) መንፈሳዊ መጽሐፎችን ማንበብ። በጣም ብዙ መንፈሳዊ መጽሐፎች ስላሉ እነዚያን በማንበብ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታችንን ልናሰፋና ለስብከት የሚጠቅሙ ማቴሪያልስ ማከማቸት እንችላለን። እነዚህ የምናነባቸውን መጻሕፍት እንዳሉ ገልብጦ ለመስበክ ሳይሆን ያገኘነውን ሃሳብ በዝግጅታችን ውስጥ አስገብተን በመጠቀም

የራሳችን የሆነ አቀራረብ ለማድረግ ይጠቅማል።

መ) የመንፈስ ቅዱስ ምሪት። ሰባኪ ከሁሉ ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ መታመንና የእርሱን ምሪት በጸሎት መፈለግ አለበት። እስከ አሁን የዘረዘርናቸውን ሁሉ አድርገን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ባንፈልግ ትክክለኛና ለህዝቡ አስፈላጊ የሆነውን የጊዜውን ቃል ማቅረብ አንችልም። ቀደም ሲል የዘረዘርናቸውን ዲሲፕሊን ሁሉ ተከትሎ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚታመን ሰባኪ ፈጽሞ የሚሰብከውን ነገር አያጣም። ስብከትን ለመቀበልም ሆነ የተቀበሉትን ሃሳብ አወቅሮ ከምሰባክ በሀይል ለመሰበክ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብቻ መተማመን ያስፈልጋል። ያለመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ምንም ማድረግ አይቻልም።

ሠ) በጥቅሱ (text) እና ከዚያ የሚወጣውን ሃሳብ ማስተማር መቻል አለመቻላችንን ማረጋገጥ። አቅምንና ችሎታን ማወቅ ጠቃሚ ነው። ዳዊት የሳያልን የጦር ልብስ ለብሶ ጐልያድን ለመውጋት ጦር ሜዳ መሄድ እንዳላስፈለገው ሁሉ ሰባኪም ከዕውቀቱና ከማስረዳት ችሎታው በላይ የሆነውን ሃሳብ የያዘ ጥቅስ (text) ለስብከቱ ፈጽሞ መምረጥ የለበትም። የተረዳውንና ያወቀውን ብቻ ነው መስበክ ያለበት። ከአቅሙ በላይ የሆነውን ሃሳብ እድገቱ ያንን የመረዳት ደረጃ ላይ ሲደርስ የዚያን ጊዜ መስበክ ይችላል። ያለዚያ ለሰዎች ነገሩ እንዲገባ ከማድረግ ይልቅ የበለጠ እንዲያደናግር ያደርጋል። ማስተማር የማንችለውን ሃሳብ ለማስተማር መሞከር ለብንም።

ረ) የሚመረጠው ጥቅስ ወይም አረፍተ ነገር ግልጽ መሆን አለበት። የተመረጠው ጥቅስ ወይም አረፍተ ነገር ግልጽ ካልሆነ ሰዎች ለማድመጥና ለመከታተል ያላቸውን ፍላጐት ይገድላል።

ሰ) የታወቁትን ጥቅሶች የታወቁ ናቸው በማለት አለመተው። የታወቁትን ጥቅሶች የታወቁ ናቸው በሚል ምክንያት አለመምረጥ ለሰባኪውና ለጉባዔው ብዙ በረከት ከሚሰጡ ጥቅሶች ሊያርቅ ይችላል። ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል 3፥16 እና ማቴዎስ 11፥28 የመሳሰሉት ጥቅሶች በታም የታወቁ ናቸው። ስለዚህ ሰዎች የሚያውቁት ጥቅስ ቢሆንም ልንሰብክበት ይገባል።

ሸ) ብሉይን ወይም አዲስ ኪዳንን አለመተው። አንዳንድ ሰዎች የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ሌሎች ደግሞ የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት በልማድ ይተዋሉ። አንዳንዶች ይህን የሚያደርጉት ከቤተ እምነታቸው ዶክትሪን የተነሳ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ደህንነት በጸጋ እንደሆነ የማያምኑ ክፍሎች ብዙ ጊዜ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቸል ይላሉ። ስለዚህ ሁሌ ከብሉይ ኪዳን ይሰብካሉ። አንዳንድ ቤተ እምነቶች ደግሞ (ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት (Church of Christ) ብሉይ ኪዳንን እንደ ታሪክ እንጂ እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለማይቀበሉት ለመመሪያና ለትምህርት የሚመረኰዙት በአዲስ ኪዳን ላይ ብቻ ነው። ሌሎች ደግሞ ከሁለቱም አንዳንድ መጽሐፎችን መርጠው ይተዋሉ። ለምሳሌ መኃልየ መኃልይን ስለሚያፍሩበት ብቻ ሆነ ብለው የሚተውት አሉ። ስለዚህ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን በረከት እንዳናጣ ስብከታችንን በ66ቱም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ላይ መመሥረት አለብን።

ቀ) ተገቢ ያልሆኑ ጥቅሶችን ከመምረጥ መጠንቀቅ። የአንዳንድ ሰዎች ጥቅስ (text) ምርጫ ለመልእክቱ የተገባ ስላይደለ የአድምጩን የመስማት ፍላጐት ይዘጋል። ስለዚህ እንዲህ ያለ ምርጫ ለአለማድረግ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ሰባኪው የሚሰብከው በዳኝነት ሙያ ላይ ለተሰለፉ ዳኞች ከሆነ ከተራራው ስብከት "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ።" የሚለው ጥቅስ እንደ text መጠቀሙ አግባብ ያለው ምርጫ አይሆንም። ዳኝነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለ ሙያ ነው። ሰለሞንም ትልቅ ጥበብ ከእግዚአብሔር የጠየቀው በትክክሉ መዳኘት እንዲችል ነው። ለዳኞች ለመሰበክ ይህንን ጥቅስ መምረጥ ግን ዳኞቹ ስብከቱን እንዳያደምጡ ፍላጐታቸውን ይዘጋል፤ ስብከቱም የተሳሳተ ይሆናል። "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ።" የሚለው ጥቅስ ሊሰበክበት የሚችልበት ቦታና ሁኔታ አለ። በዚህ በጠቀስነው ምሳሌ ውስጥ ከሆነ ግን ሊመረጥ አይገባውም። ወንጌልን ላላወቁና ገና ላላመኑ ስለደህንነት የሚናገሩትን ጥቅስ በመምረጥ ፈንታ "በአዲስ ቋንቋ መናገር" የሚለውን መምረጥ ስህተት ነው። ለምሳሌ፥ ልጆች ሆነን አንዱ ለወላጅ አባቱ እመሰክራለሁ ብሎ በልሳን ተሞልቻለሁ ይሄው ላሳይህ ብሎ ያደረገው ስህተት አለ። አባቱም አልሰሙትም።

በ) እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች የተናገሩትንና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ቃሎች በሌላ ቦታ ያንን ሃሳብ የሚደግፉ ሌሎች ጥቅሶች ከሌሉ ለስብከትህ text አድርገህ አትጠቀምበት።

ለምሳሌ፥ የኢዮብ ጓደኞች የተናገሩት ቃል፣ የፈሪሳውያን ንግግርና የመሳሰሉት። እነዚህ ሰዎች ስማቸውና ድርጊታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ቢሆንም ሐሳባቸው ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር አብሮ ሊሄድ የማይችል ስለሆነ ሀሳባቸው በሌላ ቦታ መረጃና ድጋፍ ካላገኘንለት በቀር የእነርሱን ቃሎች ለስብከት ጥቅስ አድርገን መውሰድ አይገባም።

ተ) አጠያያቂ ጥቅሶችን አለመምረጥ። አንዳንድ ጥቅሶች አጠያያቂ ከመሆናቸው የተነሳ ስብከት ሊመሠረትባቸው አይችሉም። የሐንስ 9፥31 ላይ እውሩ ሰው የተናገረውን ቃል ለምሳሌነት ብንወስድ "እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደማይሰማ እናውቃለን።" ይላል። የዚህ እውር ሰው ንግግር ፈጽሞ እውነት መሆን አይችልም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችንም ይሰማል። ከብዙ ማስረጃዎች ውስጥ አንድ ብቻ መጥቀስ ቢያስፈልግ እግዚአብሔር የቀራጩን ፀሎት እንደሰማ ከሉቃስ ወንጌል መጥቀስ ይቻላል። እግዚአብሔር የዚህን ኃጢአተኛ ቀራጭ ጸሎት ሰምቶአል። ስለዚህ ጥቅስ ስንመርጥ ጥቅስን ከጥቅስ ጋር ማስተያየትና የተናጋሪውን ማንነት የታሪኩንም ሃሳብ ሁሉ መርምረን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ቸ) የተዘነጣጠለ ጥቅስ አለመጠቀም። የፀሐፊውን ወይም የተናጋሪውን ሙሉ ሃሳብ የማያንፀባርቁ የጥቅስ ጉማጆች ለስብከት መመስረቻ ጥቅስ ሊመረጡ አይገባም።

ምሳሌ፥ “ሰዎች ሁሉ ውሸተኛ ናቸው።” ሮሜ 3፥4 ፣ “እግዚአብሔር የለም” መዝሙር 14፡1

እነዚህ ጥቅሶች ተኀርደው የወጡ በመሆናቸው የተገለፀውን ሙሉ እውነት አይናገሩም። ግማሽ እውነት ከውሸት የበለጠ አደገኛ ነው። ሰይጣን በመጀመሪያ ሲዋሽ የተናገረው ግማሽ እውነትን ነው።(ዘፍጥረት 3፥ 1-8)ሰይጣን የመጀመሪያውን ሰዎች አዳምና ሔዋንን በሰጣቸው ግማሽ እውነት ከትልቅ ጥፋት ላይ ጣላቸው። ስለዚህ የእውነት ቁራጭ ቢሆንም እንኳን ጉማጅ ጥቅሶችን ስናይ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግና ስብከት እንዳንመሰረትባቸው መጠንቀቅ ይገባል።

ኀ) ጥቅሱን በጥንቃቄ መተርጐም። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክሉ መተርጐም ከሰባኪ የሚጠበቅ ግዴታ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች እንዴት መተርጐም እንደሚገባን የሚገልጽ መመሪያ አለ። ወደፊት “የጥቅስ (text) አተረጓጐም መመሪያ” በሚል ርዕስ ስር ስለዚህ በስፋት እንመለከታለን። በዚህ ስፍራ የምንጠቅሳቸው ምሳሌዎች ግን ጥቅስን በጥንቃቄ መተርጐም እንደሚያስፈልገን የሚያሳዩ ብቻ ናቸው።

ዮሐንስ ወንጌል 3፥ 13 ጥቅሳችን ቢሆን ይህ ጥቅስ “ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም።” ይላል። ይህንን ጥቅስ እንዴት እንተረጉመዋለን? በጥንቃቄ ለመተርጐም እርምጃ ካልወሰድን ትርጉሙ “ከሰማይ ከወረደው ከኢየሱስ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም” ማለት ይሆናል፤ እንደዚህ ቢተረጐም ደግሞ ነገሩ እውነት አይሆንም። ከኢየሱስ በቀር ሌላ ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለምን? ሄኖክስ? ኤልያስስ? እነዚህ ሁሉ ወደ ሰማይ ወጥተው የለምን? ከወጡ ደግሞ ዮሐንስ ወንጌል 3፥13 ታዲያ ምን ማለት ነው? የዚህ መልሱ የሚገኘው በጥንቃቄ በመተርጐም ነው። የዮሐንስ ወንጌል 3፥13 “ወደ ላይ የወጣ የለም።” ነው የሚለው “በመውጣትና” “በመወሰድ” መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ኤልያስና ሄኖክ በራሳቸው ኃይል እንደ ክርስቶስ ወደ ሰማይ አልወጡም (አላረጉም) ነገር ግን እግዚአብሔር ወሰዳቸው። ኤልያስና ሄኖክ ተወሰዱ እንጂ በራሳቸው አልወጡም። እንደዚህ አድርገን በትክክሉና በጥንቃቄ ሳንተረጉም ከዮሐንስ ወንጌል 3፥ 13 ተነስተን ብንሰብክ ትልቅ ስህተት ውስጥ እንገባለን። ስለዚህ የምንሰብክበትን ጥቅስ (text) ከዋናው መንደርደሪያ ሃሳብ ጋር (context) አብሮ በመመልከት የፀሐፊውን የመጀመሪያ ሃሳብ ለማግኘት የአተረጓገም (hermeneutics) ሕግን መከተል ያስፈልጋል።

ጥቅስን ከመንደርደሪያው ሃሳብ ከገነጠሉትና ከሌላ ጥቅስ ጋር የአተረጓጐምን ሕግ ሳይከተሉ ከቀጠሉት ችግር ይፈጥራል። ለምሳሌ የሐዋርያት ሥራ 1፥24 ወስደው ከዮሐንስ ወንጌል 11፥16 ወይም ከሉቃስ 10፥ 28 ጋር ቢቀጥሉት እንደ ይሁዳ አንተም ራስህን ስቀል የሚል መልእክት ይሰጣል።

ከመንደርደሪያው ሃሳብና የመጀመሪያው ፀሐፊ አእምሮ ውስጥ ከነበረው ሃሳብ ከተወጣ አንድ ጥቅስ ሳይገነጠል እንኳን በራሱ የሚያዳልጥ ትርጉም ያመጣል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ብዙ ሰዎች 2ኛ ቆሮንቶስ 3፥6 ላይ “ፊደል ይገድላል” የሚለውን ጥቅስ የእግዚአብሔርን ቃል ከማወቅ ጋር አያይዘውት ቃሉን ማወቅ ይገድላል፤ መንፈስ ብቻ ነው የሚያስፈልግ ሲሉ መስማታችን ነው። ጳውሎስ ግን “ፊደል ይገድላል” ሲል በአእምሮው የነበረው ሃሳብ ስለ ኦሪት ሕግ ነው።

መክብብ 1፥ 4 በመጥቀስ “ምድር ለዘላለም ናት” ምድርን እንደወርሳለን በማለት የይሖዋ ምስክሮች ነን ባዮች የተሳሳተ ትምህርት ያስተምራሉ። ኢሳያስ 41፥14 ከመንደርደሪያው ሃሳብ ከገነጠሉት ሰው ከትል መጣ ብሎ ያሳምናል። ስለዚህ እዚህ ሁሉ ስህተት ውስጥ ላለመግባት ጥቅሶችን በጥንቃቄ መተርጐም አስፈላጊ ነው።

ነ)ተገቢ ያልሆነ መንፈሳዊ ትርጓሜ (Spiritualization) አለማድረግ። የዮሐንስ ወንጌል 10 ላይ ጌታ “እኔ በር ነኝ።” ያለውን በምናውቀው በቤት በር መተርጐም አንችልም። ክርስቶስ “በር ነኝ” ሲል ከእሱ በቀር ካልሆነ ወደ አብ የሚመጣበት እንደሌላ መጥቀሱ ነው። ስለዚህ ከእንጨት፣ ከብረት ወዘተ የተሰራውን በር ነው ማለት ሳይሆን የበር አገልግሎትን በማሰብ መንፈሳዊ ትርጉም እንሰጠዋለን። “እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ” ሲልም ቃሉን በጥሬ ትርጉም መተርጐም አይቻልም። ሣራና አጋር በሕግ ባርነትና በፀጋ ሥር ላሉት ምሳሌ ሆነው በመንፈሳዊ አተርጓጐም በጳውሎስ መልእክት ውስጥ ቀርበዋል። ነገር ግን መንፈሳዊ ትርጉም ስንሰጥ ሥርዓቱንና ገደቡን ካላወቅን ብዙ ስህተት ለማድረግ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ሁሉ በቀጥታ ከመተርጐም ይልቅ ሁልጊዜ መንፈሳዊ አተርጓጐም ልንሰጣቸው አንችልም። ለሁሉ ጥቅሶች መንፈሳዊ ትርጉም መስጠት (Spiritualizing texts) በጣም አደገኛ ነው። ቅዱስ አውግስቲን (St. Augustine) ከሚነቀፍበት አንዱ በዚህ አይነት አተርጓጐም (Spititualizing) ብዙ ስህተት ማድረጉ ነው። ኖህ ስክሮ እርቃነ ሥጋውን የተኛበትንና አንዱ ልጁ አይቶት ሲስቅ ሌላው ወደኋላው ሄዶ ጨርቅ ያለበሰበትን ታሪክ ወስዶ ስለ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ውርደት (የመሰቀል እፍረት)በማለት ሰብኮበታል። አውግስቲን ይህንን መጥፎ ዓይነት ትርጉም በመስጠቱ እስከዛሬ ድረስ በሰዎች ይነቀፋል። ሌሎችም በዚህ አይነት አተረጓጐም ምክንያት ብዙ ስህተት ያደረጉ ከተራ ስህተትም አልፈው ኑፋቄንም ያስተማሩ ሰዎች አሉ። ስለዚህ በጥቅስ አተረጓጐም ላይ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## የጥቅስ (text) አተረጓጐም መመሪያ

የአንድን ጥቅስ ትክክለኛ ትርጉም ለማወቅ የሚከተሉትን የአተረጓጐም መመሪያዎች መከተል ያስፈልጋል።

ሀ) የጥቅሱ ቃል ሥዕላዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን አስቀድሞ ማወቅ። አንድ ሰባኪ ያንድን ጥቅስ ቃል ትርጉም ለማወቅ አስቀድሞ የጥቅሱ ቃል እንዳለ የሚተረጉም ወይም ሥዕላዊ ሃሳብ እንደሆነ መመርመርና ማወቅ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመንደርደሪያው ሃሳብ አማካኝነት የአንድን ጥቅስ ትርጉም ምን እንደሆነና አተርጓጐሙም ስዕላዊ

ወይም እንዳለ የሚወሰድ መሆኑን ይወስናል። ስለሆነም ሰባኪው ከሁሉ አስቀድሞ ፀሐፊው ቃሉን በጻፈ ጊዜ በአእምሮው የነበረው የመጀመሪያው ሃሳብ ምን እንደነበር ለማወቅ መጣር ይገባዋል። ያንን ማወቅ ቃሉ እንዳለ የሚተረጉም ወይም ሥዕላዊ መሆኑን ለመወሰን ይጠቅመዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ይህንን መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አስነሳዋለሁ።” ሲል ሥዕላዊ ቃላት መጠቀሙ ነው። ሥዕላዊ ቃላት መጠቀሙን እንዴት እናውቃለን? የሐንስ ወንጌል 2፥ 19፣ 21-22 ብንመለከት የሐንስ ጌታ የተናገረው በሥዕላዊ ቃላት እንደሆነ ራሱ ግልጽ ያደርገዋል። እነዚህን ጥቅሶች ሁሉ በመመልከቱ ሃሳቡ እንዳለ የሚተረጉም ማለትም በጊዜው የነበረውን የመቅደስ ሕንፃ ስለማፍረስ እንዳልተናገረ እንረዳለን። እንደዚሁ ደግሞ (የማቴዎስ ወንጌል 26፥ 26-27 እና ማርቆስ 14፥22-24 ሉቃስ 22፥ 19-20 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥ 23-26)ላይ ያሉትን ጥቅሶች ስንመለከት በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ላይ ስለምንበላውና ስለምንጠጣው ኅብስትና ወይን እንደሚናገሩ እንገነዘባለን። ጌታ “ሥጋዬን እና ደሜን” ሲል ለተቆራረሰው ሥጋውና ለፈሰሰው ደሙ መታሰቢያ ስለሆነው ነገር መናገሩ ነው። ኅብስቱና ወይኑ ሥጋውንና ደሙን የሚያሳስቡ ሥዕላዊ ሃሳቦች ናቸው። በሌላ ቦታ ደግሞ “መታጠብ” የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሁለቱም መንገድ ማለት በሥዕላዊ እና እንዳለም በሚተረጉም ሃሳብ ቀርበዋል፤ ለንእማን በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ በመጥለቅ እንዲታጠብ ሲነገረው ያ ሥዕላዊ ሃሳብ አይደለም ንእማን እንደተባለው ውኃው ውስጥ መጥለቅ ነበረበት። የሚተረጎመው እንዳለ ነው። ነገር ግን 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥ 11 ላይ እንደተፃፈው ስለ አማኞች መታጠብ የተጻፈው ቃል ግን ሥዕላዊ ቃል ስለሆነ እንደ በፊቱ እንዳለ መተርጐም የለበትም። ቃሉ የሚናገረው አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከኃጢአታቸው ስለመታጠባቸውና ስለመንጻታቸው ነው። ስለዚህ አንድን ጥቅስ ለመተርጐም ከምንመለከታቸውና ከምንመረምራቸው ሃሳቦች አንዱ ቃሉ ሥዕላዊ እንደሆነና እንዳልሆነ መመርመር ነው።

ለ) የአንድን ቃል ትርጉም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች ምን ለማለት እንደተጠቀሙበት መመርመር። የተለያዩ ፀሐፊዎች ሁሉ ለአንድ ቃል ተመሳሳይ ትርጉም አይሰጡም። እያንዳንዱ ፀሐፊ ያንኑ አንድ ቃል የተጠቀመበት የራሱ መንገድ አለው። ለምሳሌ “እምነት(faith) “ የሚለውን ቃል በ(ገላትያ 1፥23)፣ (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥ 9- 4፥ 1) እና (የሐዋርያት ሥራ 24፥24) ላይ የተሰጠው ትርጉም የወንጌሉን ምሥራች ማመን ማለት ነው። በክርስቶስ ማመን ትልቅ የክርስትና ትምህርት ነው የሚል ነው። ሮሜ 3፥3 ላይ ደግሞ ያለው እምነት የሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም “እውነት” ወይም “ታማኝነት” የሚል ነው። እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ ይገልጻል። የሐዋርያት ሥራ 17፥31 ላይ ደግሞ እምነት የሚለው ቃል የግሪኩ ቃል ትርጉም “ዋስትና (assurance) የሚል ነው። በተለያየ ቦታ ያው አንድ ቃል ልዩ ልዩ ትርጉም አለው።

እንደገናም “ሥጋ (flesh)” የሚለው ቃል (በሕዝቅኤል 11፥ 19)ላይ ከድንጋይ ተነፃፅሮ ነው የቀረበ። በ(የሐንስ ወንጌል 1፥ 14)፣ (ሮሜ 1፥ 3)፣ (ሮሜ 9፥ 3)የሚያመለክተው ስለሰብዓዊ ተፈጥሮ ነው። እዚህ ላይ ስለሰብዓዊ ተፈጥሮ ቢናገርም ኃጢአተኝነትን አይጠቅስም። በ(ሮሜ 8፥ 13ና ኤፌሶን 2፥ 3) ላይ ግን ኃጢአተኛና በስባሽ ስለሆነው የሰው ተፈጥሮ ይጠቁማል። ስለዚህ አንድን ቃል ስናነብ በዚያ ስፍራ ቃሉ የቀረበው በምን መንገድ እንደሆነ ማስተዋልና መንደርደሪያ ሃሳቡን ተመርኩዘን ትርጉሙን ማወቅ አለብን።

ሐ) ጥቅስን ከጥቅስ ጋር እያወዳደሩ መመልከት። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክሉ መተርጐም የሚቻለው በራሱ በእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛው የራሱ ተርጓሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ወጥ መጽሐፍ ስለሆነ አንድ ጥቅስ መተርጐም ያለበት ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር ነው። ስለዚህ ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት ጥቅስን ከጥቅስ ጋር በማነፃፀር መመልከት አስፈላጊ ነው።

ሠ) ቃሉ ሲጻፍ በጊዜው ቃሉ የተጻፈላቸው ሰዎች የነበራቸውን ባህልና ልማድ መርምሮ ማወቅ። እዚህ ቦታ ላይ በጊዜው የነበረውን የአይሁዶችን አለባበስ እንደምሳሌ ብንመለከት፤ አይሁዶች የሚለብሱት ሁለት ዓይነት ጨርቅ ነበር። አንደኛው እንደ ረጅም ቀሚስ ሆኖ የሚጠለቅ ሙሉ እጅጌ ያለው ልብስ ነው። ከውስጥ ገላ የሚሸፈንበት ልብስ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ረጅም የሆነ ጨርቅ ነው። ይህንን ረጅም ጨርቅ ወገብ ላይ ሰውነትን ሁሉ ይሸፍናል። ግማሹም ከወገብ በታች ያለውን አካል ይሸፍናል። አንድ ሰው በቤቱ ሲሆን ወገብ ላይ በመቀነት የሚታሰረውን ጨርቅ አይለብሰም፥ በአጠለቀው ቀሚስ ብቻ መሆን ይችላል። ነገር ግን ወገብ ላይ በመቀነት የሚታጠቁትን ልብስ ሳይደርብ ወደ ውጭ ወደ አደባባይና ሌሎች ሥፍራዎች መሄድና መታየት የለበትም። ቀሚሱን ብቻውን መልበስ በባህላቸው እንደራቁትነት ይቆጠራል። ስለዚህ ቀሜሱን ብቻ ለብሶ አደባባይ መታየት እንደራቁትነት ስለሚቆጠር አሳፋሪ ይሆናል። ስለሆንም (የሐንስ 13፥ 4፣ የሐንስ 21፥ እና ኢሳያስ 20፥2-4) ያሉትን ዓይነት ጥቅሶች ስንመለከት ትክክለኛው ትርጉም እንዲገባን በጊዜው የነበረውን ባህልና ልማድ ማወቅ ያስፈልጋል። ያለዚያ እርቃነ ሥጋ መሆን ማለት ይመስለናል።

ረ) መንደርደሪያ ሃሳቡን (context) በደንብ መመልከት። እስከ አሁን የዘረዘርናቸውን ነገሮች ከመመልከታችን አስቀድሞና በኋላም ደጋግመን መመልከት ያለብን የጥቅሱን (context) ነው። ያለዚህ እውነተኛና ትክክለኛ ትረጉም ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ ሰባኪ የጥቅሱን መንደርደሪያ ሃሳብ ፈልጐ ማግኘት አለበት። መንደርደሪያው ሃሳብ የሚገኘው ከጥቅሱ ቀደም ብለው ባሉት ወይም ወረድ ብለው ባሉት ጥቅሶች ውስጥ ነው።

ሰ)ትክክለኛና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተሳሰብ የተደገፈ ግምት መጠቀም። አንዳንድ ጥቅሶች መንደርደሪያ ሃሳቡንም ብናገኝም ምን ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ላይሆንልን ይችላል። ለምሳሌ የይሁዳን አሟሟት ሁኔታ ብንመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ግምት ካልተጠቀምን እንዴት እንደነበረ ላይገባን ይችላል። ስለ ይሁዳ የአሟሟት ሁኔታ (ማቴዎስ 27፥3-8)ባለው ክፍልና (የሐዋርያት ሥራ 1፥ 15-19) ባለው

ክፍል ያለውን ስንመለከት በመጀመሪያው ቦታ የተገለፀው ሃሳብ ይሁዳ ታንቆ እንደ ሞተ ያሳያል። በሌላ ቦታ ደግሞ ፈንድቶ እንደሞተ እናያለን። (የሐዋርያት ሥራ 1፥15-19) ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ይህንን ሃሳብ ለማስታረቅና በትክክሉ የሆነውን ለማወቅ የምንችለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግምት ስናደርግ ነው። ይሁዳ በማቴዎስ ወንጌል እንደተጻፈው የሞተው ተሰቅሎ ነው። ሰው የሚሰቀለው ዛፍ ላይ በገመድ ተንጠልጥሎ ነው። ሉቃስ (የሐዋርያት ሥራ 1)ላይ ደግሞ መፈንዳቱን ይነግረናል። ይሁዳ የተሰቀለበት ገመድ የተበጠሰ ሊሆን ስለሚችል ነው። ከተሰቀለ በኋላ የተሰቀለበት ገመድ ክብደቱን መያዝ ስላልቻለ ስለተበጠሰ ወይም ገመዱ የታሰረበት ቅርንጫፍ ስለተቆረጠ ይሁዳ ሲወድቅ ከሥር ከነበረው ድንጋይ ይሁን ጉቶ ወይም ሌላ ነገር ላይ ሲወድቅ ሆዱ ሳይፈነዳ አይቀርም አንጀቱ ተዘርግፎ መሞት የሚችለው በዚህ ሁኔታ ነው። ስለዚህ ይህን ዓይነት ትክክለኛ ግምት ስናደርግ በሁለቱ ጥቅሶች መካከል ስለይሁዳ አሟሟት ሁኔታ የተገለፀውን ተቃራኒ የሚመስል ሃሳብ ለማስታረቅ እንችላለን።

ሸ) ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉትን ሁለተኛ ምንጮች (Secondary re-sources) መመልከት። በመጀመሪያ በቃሉ ውስጥ ከላይ እንደተዘረዘረው ስለዚያ ጥቅስ ያለውን ሃሳብ ከተመለከትንና ካጠናን በኋላ ተጨማሪ ሃሳብ ለማግኘት ሌሎች ሰዎች ያንን ጥቅስ እንዴት እንደተረጎሙት የአነርሱን ሃሳብና ትርጉም መመልከት አስፈላጊ ነው። እነዚህም የሚገኙት ኮንኮርዳንስ፣ ኮሜንታሪ፣ ልዩ ልዩ መጽሐፎች፣ ታሪኮች፣ ስብከቶች ወዘተረፈ ስንመለከት ነው።

## መልመጃ (Exercise)

ለሚከተሉት መልእክቶች ተስማሚ የሆነ ጥቅስ ምርጥላቸው።

የወንጌል መልእክት (ላልዳኑ ሰዎች)

የጋብቻ መልእክት

የለቅሶ መልእክት

የአባቶች ቀን መልእክት

የእናቶች ቀን መልእክት

የአዲስ ዓመት መልእክት

ለወንጌል አገልጋዮች የሚሆን መልእክት

ዶክትሪናል መልእክት

ርዕሳዊ ስብከት (Topical Sermon)

ርዕሳዊ ስብከት (topical sermon) የምንለው የስብከቱ ልዩ ልዩ ክፍሎችና ሐሳቦች ከጥቅሱ (text) ሳይሆን ከርዕሱ የሚመነጩ ሲሆን ነው። ይህም ማለት፥

ሀ) ርዕሳዊ ስብከት የሚጀምረው በርዕስ ወይም በአንድ መሪ ቃል (theme) ሲሆን የስብከቱ ልዩ ልዩ ንዑስ ርዑሶችና ሃሳቦች የሚመነጩት ከርዕሱ ይሆናል።

ለ) ስብከቱ የሚመሰረትበት አንድ የተወሰነ ጥቅስ (text) አይኖረውም። ሆኖም ግን የትምህርቱ ሃሳብ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ላይ ያተኮረ ነው።

ሐ) ርዕሳዊ ስብከት ሊኖረው የሚችለው አንድ ማዕከላዊ ሃሳብ ብቻ ነው። እያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ የሚያተኩረው በብዙ ልዩ ልዩ ሃሳቦች ላይ ሳይሆን በማዕከላዊ ሃሳቡ ወይም በስብከቱ ዋና ዓላማ ላይ ነው።

## የርዕሳዊ ስብከት ምሳሌ

የፀሎት ኃይል፣ የአማኝ ተስፋ፣ የሰይጣን ውሸት፣ የጥፋት ውሃ፣ የተከፈተ ሰማይ፣ የኢየሱስ ምሳሌዎች፣ ልጓም ለቆ ቼቼ ... ወዘተ።

## የርዕስ አመራረጥ

ሰባኪ የሚሰብክበት ርዕስ እንዲሰብክ የጋበዙት ሰዎች ሊሰጡት፤ ወይም ወቅታዊ ከሆኑት ሁኔታዎችና በዓላት (ገና፣ ፋሲካ ወዘተ) ሊያገኝ ይችላል። አንድ ሰባኪ በፀሎት መንፈስ ቅዱስ የሚሰብክበትን ርዐስና ሃሳብ እንዲሰጠው መጠየቅ ይገባዋል።

ሀ) የስብከት ርዐስ ስብከቱ በምን ሃሳብ ላይ እንዳተኮረ የሚገልጽ መሆን አለበት።

ለ) የስብከት ርዐስ ያድማጮቹን የመስማት ፍላጐት የሚቀሰቅስና ማራኪ መሆን አለበት።

ለምሳሌ - "ልጓም ለቆ ቼቼ" "እንባጥ ብሎ ወደ ኋላ መዝለል " ... ወዘተ የመሳሰሉትን የዚህን ፅሑፍ አዘጋጅ የቆዩ ስብከቶች ብዙ ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ እንደሚያስታውሱአቸው ይናገራሉ።

ሐ) የስብከት ርዕስ አጭር መሆን አለበት።

መ) ርዕስ ሐሳቡን በቀጥታ በመግለጽ፣ ወይም በጥያቄ መልክ ወይም በቃለ አጋኖ መልክ ማቅረብ ይቻላል።

ሠ) ርዕስ ማራኪ መሆን ቢገባውም የመድረኩን ክብር የሚቀንስ ቃላት ያዘለ መሆን የለበትም።

ርዕሱ ከተመረጠ በኋላ ንዑስ ርዕሶቹና ሃሳቦች ሁሉ ከርዕሱ ይመነጫሉ።

ርዕስ - የክርስቲያን ተስፋ ባህሪያት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ሕያው ተስፋ ነው | 1ኛ/ጴጥሮስ 1፥3 |
| 2. | የሚያድን ተስፋ ነው | 1ኛ/ተሰሎንቄ 5፥-8 |
| 3. | እርግጠኛ የሆነ ተስፋ ነው | ዕብ 6፥19 |
| 4. | መልካም ተስፋ ነው | 2ኛ/ተሰሎንቄ 2፥13 |
| 5. | የተባረከ ተስፋ ነው | ቲቶ 2፥13 |
| 6. | ዘላለማዊ ተስፋ ነው | ቲቶ 3፥7 |

እነዚህ ሁሉ ንዑስ ሃሳቦች ማዕከላዊውን ሃሳብ (ርዕሱን) የሚያብራሩና የሚያጠናክሩ ናቸው።

 © 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas 

## መልመጃ(Exercise)

ለወንጌል መነቃቂያ ስብከት የሚሆኑ 5 አርዕስቶች ምረጥና ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ርዕስ ወስደህ የስብከትህን አስተዋጽኦ (outline) ሥራ።

## በማስፋፋትና በመተንተን ዘዴ የሚቀርብ ስብከት (Expository Sermon)

ኤክስፖዚተሪ ስብከት ባንድ መጽሐፍ፣ በአንድ ምዕራፍ፣ በአንድ ታሪክ፣ በአንድ ፓራግራፍ … ወዘተ ላይ ሊመሠረት ይችላል። ኤክስፖዚተሪ ስብከቱ የተመሠረተበትን ሃሳብ ወይም ክፍል በመተርጐም በማብራራትና በማስፋፋት ማስተማር ላይ ያተኰረ ነው። የስብከቱ ልዩ ልዩ ሃሳቦች ከዋናው ርዕስ የሚመነጩና ከዚያ የሚዳብሩ ሀሳቦች ናቸው።

በማብራራትና በመተንተን ላይ የተመሰረተ (exposition) ስብከት ምሳሌ

ሀ) መንፈሳዊ ጦርነት (ኤፌሶን 6፥10-18)

- የክርስቲያን ሞራል — ቁጥር 10-13
- ከፍ ያለ ነው። — ቁጥር 10
- የበረታና የፀና — ቁጥር 11-13
- የክርስቲያን ዕቃ ጦር — ቁጥር 14-17
- መከላከያ መሣሪያዎች — ቁጥር 17
- የማጥቂያ — ቁጥር 17
- የክርስቲያን የፀሎት ሕይወት
- የማይቋረጥ መሆን አለበት — ቁጥር 18
- የምልጃ መሆን አለበት — ቁጥር 18

## የማብራራትና የመተንተን (የኤክስፖዚተሪ) ስብከት አዘገጃጀት መመሪያ

ሀ) ስብከቱ የሚመሠረትተን ክፍል በጥንቃቄ ማጥናትና የሰብከቱ ሃሳብ ያለበት ጥቅስ የተዋቀረባቸውን ቃላት ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

ለ) ስብከቱ የተመሠረተበት ክፍል ውስጥ ሰፊ ሃሳብ የያዘው ነገር ርዕስ ሊወጣበት ይችላል።

ሐ) የስብከቱ አስተዋጽኦ (outline)ከስብከቱ ክፍል ቅደም ተከተል ባለው መንገድ (in a chronological way)መውጣትና መዳበር ይኖርበታል።

መ) በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ዋና ዋና እውነቶች ያስተዋጽኦው ዋና ዋና ክፍሎች መሆን ይችላሉ።

## መልመጃ(Exercise)

ርዕሱን፣ ማዕከላዊ ሃሳቡንና ንዑስ ክፍሎቹን ያካተተ የስብከት አስተዋፅዖ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13፥ 1-8 ላይ በመመሥረት ያዘጋጁ።

የስብከት አስተዋጽኦ (outline)

የአንድ ስብከት መላ አካል የሚከተሉትን ነገሮች ያካትታል።

መግቢያ (Introduction)

አካል (Body)

መዝጊያ (Conclusion)

አንድን ስብከት ከማዘጋጀት በፊት ቀደም ሲል የዘረዘርናቸውን መመሪያዎች በመከተል በተንበረከከ ጉልበት ሃሳቡን ካጠናን በኋላ ለስብከቱ አስቀድሞ አስተዋጽኦ ማውጣት ያስፈልጋል። አስተዋጽኦ (outline) አጭር ሃሳብ ብቻ መያዝ አለበት።

ከዚህ በታች የምንመለከተው የስብከት አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ይዘት ነው።

አስተዋጽኦ (outline)

ርዕስ_______________________________________________

_______________________________

(Title)

ጥቅስ ______________________________________________

_______________________________

(Text)

መግቢያ

(Intorduction) 1. ______________________________

______________________

መሸጋገሪያ አረፍተ ነገር __________________________

______________________

(Transitional Sentence)

ዋና ሃሳብ ____________________________________________

_____________________

(First main division)

ሀ) የመጀመሪያው ዋና ሃሳብ ___________________________

__________________

(1st subdivision) ትንተና

ለ) ሁለተኛው ዋና ሃሳብ _____________________________

__________________

(2nd subdivision) ትንተና

ንዑስ ሃሳብ

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

(በዚህ ዓይነት የስብከቱ አካል የሆነውን ዋና ሃሳብ ከልዩ ልዩ ምሳሌ ጋር ተብራርቶ ይቀርባል)

መዝጊያ

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

በዚህ ቦታ ሃሳብ ተጠቃሎ ከሰሚዎች ሕይወት ጋር እንዲያያዝ ከተደረገ በኋላ መደምደሚያ ይደረግለታል።

እነዚህን ሃሳቦች ሁሉ አንድ ሰው ሲያስተምር ስብከት ሊኖረው የሚገባው ይዘት የሚከተሉን ነገሮች መሆን አለበት በማለት በሦስት መንገዶች አሳጥሮታል። እነርሱም፥

Hook (የሰውን የማድመጥ ፍላጎት በሚማርክ መንገድ መጀመር)

Book (ለመድመጥ ሲማረኩ የቃሉን እውነት መስጠት)

Took ( ህይወታቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ማድረግ) ናቸው።

## መግቢያ (Introduction)

ማናኛውም ጥሩ ስብከት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ሊኖሩት ያስፈልጋል። እነዚህም መግቢያ፣ አካልና መዝጊያ ናቸው። መግቢያ ለሁሉ ነገር አስፈላጊ ነው። መጻሕፍት ያለመግቢያ አይጻፍም። ሙዚቃም ሲደረስ መግቢያ አለው። ማንኛውም ዓይነት ለህዝብ የሚደረጉ ንግግሮች ሁሉ መግቢያ አላቸው። እንደዚሁ ስብከትም መግቢያ ሊኖረው ይገባል።

አንድ ሰባኪ አድማጮቹን ለስብከቱ አእምሮአቸውን የሚያዘጋጀው፤ የማድመጥ ፍላጎታቸውም የተቀሰቀሰ እንዲሆን ለማድረግ የሚችለው በመግቢያ ነው።

## የመግቢያ ዓላማ

መግቢያ የሚያስፈልግበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፥

ሀ) አድማጮች በምንናገርበት ርዕስ የሚሰጠውን ትምህርት የማድመጥ ፍላጎት እንዲፈጠርባቸው ለማድረግ አድማጮች ሀሳባቸው ሳይሰበጣጠር ነቅተው ስብከት ሊያደምጡ የሚችሉት መግቢያው የሚቀሰቅስና የሚማርክ ሲሆን ነው። ሰባኪው ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር መግቢያው ላይ ያሉት ቃሎች ካድማጮች ፍላጐት ጋር የተያያዙ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት። ሰዎች የማድመጥ ፍላጐታቸው (Intere-set)ካልተማረከ የሚባለውን በጥሞና መከታተልና ማድመጥ አይፈልጉም። ስለዚህ ሰባኪው በመግቢያው ላይ በአድማጮቹ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ሃሳብ መናገር አለበት። ሁሉም በማያውቁት ወይም ሊያውቁ የሚፈልጉት ነገር፤ ወይም በቅርቡ በተፈፀሙ ድርጊቶች፤ ወይም ሁሉም በሚያውቁት ዜና ... ወዘተ መግቢያ ሲጀመር ዋናው ሃሳብ ምን ይሆን? በማለት ሰዎች ስብከቱን በሙሉ ለመከታተል በጉጉት ይጠብቃሉ።

ለ) በርዕሱ የምናቀርበው ሃሳብ እንዲገባቸው ለማድረግ

መግቢያ ከመልእክቱ ዓላማ ጋር ሲያያዝ አድምጩ መከታተሉን አያቆምም። ስብከት መግቢያ ከሌለው ይበላሻል። ለምሳሌ የምንሰብከው ስለክርስቶስ የፍርድ ወንበር ቢሆን ዘለን "አንዱ ይወቀሳል ሌላው አክሊል ያገኛል" ብንል ስለምን እንደምንናገር ለሰዎች አይገባም፤ ነገሩንም ለመከታተል አይፈልጉም። መግቢያ የሚያስፈልገው እንዲህ ያለውን ችግር ለማጥፋት ነው።

## የመግቢያ ምንጭ (Sources of an introduction)

ከሚከተሉት ምንጮች መግቢያ ማግኘት ይቻላል።

ሀ) ስብከቱ ከተመሰረተበት ጥቅስ (Text)

ብዙ ጊዜ ለመግቢያ የሚሆን ጥሩ ሃሳብ ትምህርቱ ከተመሠረተበት ጥቅስ ይገኛል።

ለ) ከመንደርደሪያ ሃሳብ (Context)

ሐ) ከታሪካዊ አቀማመጡ (Historical setting)

ለምሳሌ ስለ ኢሳይያስ ራዕይ ከኢሳያስ 6 ለመስበክ ቢፈልጉ ኢሳይያስ ስለኖረበት ዘመን የፖለቲካና የሥነ ምግባር (moral) ሁኔታ (2ኛ ዜና 26) መግለጽ ይቻላል። በተጨማሪም ኢሳይያስ ያደንቀው ስለነበረው ንጉሥ ዖዝያንና አሟሟቱ እግዚአብሔርን በንጉሥነቱ ግርማ እንዴት እንዳየ... ወዘተ መጥቀስ ይቻላል።

መ) ስለስፍራው የጂዖግራፊ አቀማመጥ

ቃሉ ሲነገር የተነገረበት ስፍራ አቀማመጥ በሚጠቅስ መግቢያ መጀመር ይቻላል። ለምሳሌ ክርስቶስ በታቦር ተራራ ላይ ስለመለወጡ፤ ስለፈተናው፣ ወይም ስለሞቱ ለመስበክ ብንፈልግ ድርጊቱ ስለተፈፀመበት ሥፍራ አቀማመጥና ሁኔታ መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

ሠ) በጊዜው ስለነበረው ባህልና ልማድ

ረ) ስለወቅት

ወቅታዊ ስብከት ስናቀርብ ስለዚያ ወቅት መናገር ያስፈልጋል። ለምሳሌ በገናና በፋሲካ ወይም በአንድ የተለየ ሁኔታ መልእክት ስናቀርብ ስለዚያ የተለየ ወቅት በመጥቀስ መጀመር ይቻላል።

## የጥሩ መግቢያ መመሪያ

ሀ) መግቢያ አጭር መሆን አለበት። አንድን መጽሐፍ ለማንበብ መግቢያ አስፈላጊ ነው። የመግቢያው ርዝመት ግን አሥር ወይም ሃያ ገጽ ቢሆን አንባቢዎች መግቢያውንም መጽሐፉንም ለማንበብ ያላቸውን ፍላጐት ያጠፋዋል። ስለዚህ መግቢያ ሁልጊዜ አጭር ሊሆን ያስፈልጋል።

ለ) ከምናስተምረው ሃሳብ ጋር የተዛመደ ሊሆን ይገባል።

ሐ) ማራኪ ሊሆን ይገባል

መ) ገለፃ በሚጠይቅ ከባድ ሃሳብ መጀመር የለበትም

## የስብከት ዋና አካል (Body of the Sermon)

የአንድ ስብከት መግቢያ አድማጮች ስብከቱን ለመስማት ፍላጐት እንዲኖራቸው ሊቀሰቅስ ወይም ፍላጐታቸውን ሊዘጋ ይችላል። የአንድ የስብከት አካል ደግሞ አድማጮቹ የሰሙትን ሊያስታውሱት የሚችሉት ወይም የሚረሱት እንዲሆን ያደርጋል። የስብከት ግቡ ሰዎች የሰሙትን ሳይረሱ በሕይወታቸው ለውጥ ለማምጣት እንዲጠቀሙበት ነው። ስለሆነም የሰሙት ስብከት የሚረሳ ሳይሆን የሚታወስ እንዲሆን መጣር የሰባኪው ኃላፊነት ነው።

የስብከት አካል በርዕሱ የተገለፀው ዋናው የስብከቱ ፍሬ ሃሳብ የሚገለጽበት ቦታ ነው። የመልእክቱ ዋና ዋና ነጥቦች የሚተነተኑትና የሚብራሩት በዚህ ክፍል ነው። የስብከት ርዕስ ወይም መሪ ሃሳብ (theme)የስብከቱን ግብ ይወስናል። ነገር ግን ይህ የተወሰነው ግብ የሚገለፀውና የሚብራራው በስብከቱ አካል ነው። የስብከቱ አካል በትክክል ካልተዘጋጀና ካልቀረበ ሰባኪው ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ምንም ተስፋ እንደሌለውና በምድረ በዳ እንደሚዞር መንገደኛ ይሆናል። ስለዚህ የስብከት አካል በዋና ዋና ርዕሶች (sub heading) ወይም ዋና ዋና ክፍሎች (main division)ሃሳቡ እየዳበረ መሄድ አለበት።

እያንዳንዱ ዋና ዋና ክፍል ደግሞ በንዑስ ክፍሎች (sub division)እየተከፈለ የመልእክቱ ሃሳብ እየተብራራና ሰዎች ሊያውቁ የሚገባቸውን ነገሮች እንዲረዱ እያደረገ ይሄዳል። የስብከት አካል ልክ እንደ ሰውነት ሲሆን ዋና ዋና ክፍሎቹ ደግሞ ልክ ሰውነትን እንደሚሸከሙትና እንደሚያበጁት አጥንቶች (skeleton)ናቸው።

ዋና ዋና ክፍሎች (main divisions)ሲዘጋጅ የስብከቱ ሃሳብ እንቅስቃሴው እየዳበረ የሚሄድና (progressive)ቅደም ተከተሉ ሥርዓታዊ (ማለት chronological or logical)ሊሆን ይገባል። እንዲህ ሲሆን አድማጮቹ የተማሩትን ሁሉ በዝርዝር ባያስታውሱትም እንኳን ዋና ዋና ነጥቦቹንና የስብከቱን ሃሳብ እንዲያስታውሱት ይጠቅማል። እያንዳንዱ ዋና ክፍል (main division)የስብከቱን ሃሳብ ይደግፋል፣ ያብራራል። እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል (sub division)ደግሞ ዋና ክፍሉን ይደግፋል።

በአንድ የስብከት አካል ውስጥ ምን ያህል ዋና ክፍል ሊኖር እንደሚገባው ሰዎች የተለያየ አስተያየት ይሰጣሉ። አንድ ስብከት ከ 3 እስከ 7 ያህል ዋና ክፍል ሊኖረው ይገባል የሚሉ አሉ። ዳሩ ግን ብዙ ሰዎች እንደሚሉትና እንደሚስማሙት አንድ ስብከት ከ 3 የበለጠ ዋና ክፍል ሊኖርው አይገባም። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ክፍል ላይ ሰባኪው 15 ደቂቃ ቢያጠፋ ለሦስቱ የሚፈጅበት ጊዜ 45 ደቂቃ ነው። በዚህ ላይ 10 ደቂቃ ለመግቢያ 10 ደቂቃ ለመዝጊያ ሲጨመርበት የስብከቱ ርዝመት 1 ሰዓት ከ 5 ደቂቃ ይወስዳል። ከዚህ የተነሳ ነው ዋና ዋና ክፍሎች ከ 3 መብለጥ የለባቸውም የሚባለው። እዚህ ቦታ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነገር ደግሞ ካንዱ ክፍል ወደሌላው ክፍል ካንዱ ንዑስ ክፍል ወደሌላው ክፍል ለመሸጋገር ጥሩ የመሸጋገሪያ ቃላት (transition)አስፈላጊነት እንዳላቸው ነው። መሸጋገሪያ (transition) ከአንዱ ሃሳብ ወደ ሌላው ሃሳብ የሚያሸጋግር እንቅስቃሴ ነው። መገጣጠሚያዎች ለሰውነታችን አጥንቶች የሚያስፈልጉትን ያህል መሸጋገሪያዎችም ለአንድ ስብከት አስፈላጊ ናቸው። ስብከቱንም አንድ ወጥ የሚያደርገው መሸጋገሪያው በጥሩ ሲቀርብ ነው። ያለ መሸጋገሪያ በስብከቱ የሚቀርቡት ነጥቦች ሁሉ የተዛመዱ አይሆኑም። ስለዚህ ስብከት ሲዘጋጅ እነዚህ ሁሉ መታሰብ አለባቸው።

## መዝጊያ (Conclusion)

መዝጊያ በስብከቱ ለቀረበው ሃሳብ ተገቢ የሆነ መቋጫ ነው። አንዳንድ ሰባኪዎች ጥሩ ስበከት ከሰበኩ በኋላ ጥሩ መቋጫ ማድረግ ይተዋሉ። አንድ መጽሐፍ ስታነቡ ቆይታችሁ፣ ታሪኩም በጣም ጥሟችሁ መጨረሻውን ለማወቅ ጓጉታችሁ ስትቀጥሉ መዝጊያ ባይኖረው (ማለት ታሪኩ ባይቋጭ) መጽሐፉን ትጥሉታላችሁ፤ ጊዜያችሁም እንደባከነ ይቆጠራል። አንድ ስብከትም የሚወድቀውና ዋጋ የሚያጣው ሰባኪው ጥሩ መቋጫ ማድረግ ሲያቅተው ነው። መዝጊያ አድማጮች ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰሙት ነገር ነው። ስለሆነም የሚከተሉት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል።

የተሰበከውን ሃሳብ ከሰሚዎች ሕይወት ጋር ማዛመድ (Application)የተሰበከውን ሃሳብ አድማጩ ለራሱ ወስዶ የማይጠቀምበት ከሆነ ዋጋ የለውም። ስለሆነም የተሰበከው ሃሳብ ላድማጮች እንዲጠቅም በስብከቱ አካል የተብራራውን ሃሳብ በግል ሕይወታቸው እንዲጠቀሙበት ሃሳቡን ወደ ልባቸው እንዲደርስ ማድረግ ይገባል። ርዕሳችን ስለ መንግሥተ ሰማይ ቢሆን ስለ መንግስተ



© 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas

ሰማይ ምንነት አብራርተን፤ ውበቱንና ድምቀቱን ገልፀን ብንተው ጥቅም የለውም። በዚህ ርዕስ የምንሰብከው ሰዎች ጉዞአቸውን ወደዚያ እንዲያደርጉና እንዲገቡ ስለሆነ የስብከቱ መዝጊያ አድማጮቹ ያንን ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚገፋፋ መሆን አለበት። የስብከቱ ርዕስ ሲያል ከሆነም የሲያልን ምንነትና መጥፎነት ገልፀን ለመተው ሳይሆን አድማጮቻችን ወደዚያ እንዳይሄዱና በክርስቶስ አማካይነት ጉዞአቸውን ወደመንግሥተ ሰማይ እንዲያቀኑ ማድረግ መሆን አለበት።

ስለዚህ መዝጊያ ለእያንዳንዱ ሰሚ መልእክቱ በግል እንዲደርስ የሚያደርግ ሊሆን ይገባል። ይህም ናታን ዳዊትን "ያ ሰው አንተ ነህ።" ብሎ ታሪኩን ወደ የግል ሕይወቱ እንደጠቆመ ማለት ነው። ጴጥሮስም የጴንጤቆስጤ ቀን በሰበከው ስብከቱ እንዲህ ሲል ስብከቱ የአድማጮቹ የግል ሕይወት ላይ እንዲያተኩር አድርጓል፥ "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእሥራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።" የሐዋርያት ሥራ 2፥36 ጴጥሮስ ከቁጥር 14 ጀምሮ የሰበከውን ስበከት የደመደመው በቁጥር 36 ነው። ሰሚዎቹም ስብከቱ ከግል ሕይወታቸው ጋር ስለተያያዘ የግል ውሳኔ ለማድረግ እንደወሰኑ ከቁጥር 37 ጀምሮ እንመለከታለን።

በተጨማሪም መዝጊያ፥ ግልጽ መሆን አለበት አጭር መሆን አለበት፥ የመዝጊያ ርዝመት ከመግቢያው የበለጠ መሆን የለበትም። ብዙ ሰዎች መግቢያ ከ 5 ደቂቃ መብለጥ የለበትም ይላሉ። ነገር ግን መዝጊያ ምን ቢባዛ ከ 10 ደቂቃ የበለጠ መሆን የለበትም።

መዝጊያ የስበከቱ መጨረሻ መሆን አለበት። ስለዚህ መዝጊያው ላይ አዲስ ነጥብ ወይም በስብከቱ ያልነበረ ሌላ ሃሳብ ማቅረብ አይገባም። መዝጊያ የሰብከቱ የመጨረሻ ግብ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ማብቃት አለበት እንጂ "አንድ ተጨማሪ ነጥብ ... " በማለት መቀጠል የለበትም።

የተለያዩ የመዝጊያ ዓይነቶች አሉ። (recapitulation, illustration, appeal or application, exhortation etc.)

## ምሳሌዎች (Illustration)

መስኮት ለቤት እንዳለው ጥቅም ምሳሌም ለስበከት ይጠቅማል። መስኮት ለቤት የሚሰራበት ምክንያት ብርሃን ወደ ውስጥ እንዲገባና እንዳይጨልም ነው። ምሳሌ በስብከት ውስጥ የምናክልበትም ምክንያት ለስብከታችን ብርሃን እንዲሰጥና የምንናገረውን ላድምጮች ግልጽ እንዲያደርግ ነው። መስኮት የሌለው ቤት ብርሃን ማጣት ብቻ ሳይሆን ውበት የለውም። መስኮት የሌለው ቤት እሥር ቤት ይመስላል። ምሳሌ ለአንድ ስብከት ብርሃን ብቻ ሳይሆን ውበትም ይሰጠዋል።

የምሳሌዎች ጥቅም

ሀ) መልእክቱ ግልጽና የሚገባ እንዲሆን ያደርጋሉ።

ሰባኪ የቱንም ያህል ለማብራራት ቢደክምም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የሚሰሙትን እውነት በቀላሉ መረዳት ይቸገራሉ። በምሳሌ ሲነገራቸው ግን የሚሰሙት ነገር ግልጽ ይሆንላቸዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶቹን ሁሉ በምሳሌዎች ለሰዎች ያስተምር የነበረው ለዚህ ነው።

ለ) መልእክቱን የሚደመጥና ጣዕም ያለው (intereseting)እንዲሆን ያደርጉታል

በምሳሌዎች ረዳትነት የሚቀርብ መልእክት አይደርቅም፤ አይሰለችምም። ምሳሌዎች አእምሮን ያዝናናሉ። የአድማጮችንም የመስማት ፍላጐት ስለሚቀሰቅሱ ሰባኪው ቀጥሎ የሚናገረውን ለማወቅ መጓጓትን ይፈጥራሉ።

ሐ) የመልእክቱ ሃሳብ እንዳይረሳ ይረዳሉ። ሰዎች በምሳሌ የተማሩትን እውነት አይረሱትም።

መ) ስሜት ይነካሉ። በምሳሌዎች የሚነገር እውነት የመስማት ፍላጐት መቀስቀስ ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ስሜት ይነካል።

ሠ) አድማጮች መከላከያቸውን እንዲጥሉ ያደርጋሉ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ጥፋታቸውና ስህተታቸው በቀጥታ ሲነገራቸው ላለመቀበል መከላከያ ያደርጋሉ። ጥፋታቸውንና ስህተታቸውን መስማት ስለማይወዱ ዙሪያቸውን በመከላከከያ ያጥራሉ። ነገር ግን ምሳሌዎችን ሲያደምጡ ሳያውቁት መከላከያቸውን ይጥላሉ። ናታን ወደ ንጉሥ ዳዊት በሄደ ጊዜ በመጀመሪያ የነገረው ምሳሌ ነው። ዳዊት መከላከያውን ጥሎ ነው የሰማው። ምሳሌዎች ይህን ለመሰለ ጉዳይ ይጠቅማሉ።

## ምሳሌዎች ለማግኘት የሚቻልበት መንገድ

ሀ) ሁሉን ነገር መመልከት (Observation)

ጌታ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበት ዘመን ሁሉን ነገር ይመለከትና ያስተውል ነበር። ያስተማራቸውን ምሳሌዎች ስንመለከት ሰዎች በቅርብ የሚያውቋቸውና የተመለከቱት ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ።

ዘር ሲዘራ፥ የገበሬውን ሥራ አስተውሎ በምሳሌ አቀረበው።

ሠርግ፥ ሠርግን በተመለከተ በትምህርቱ ብዙ ቦታ ላይ ለምሳሌነት ተጠቀመበት።

ወፎችን፣ የምድር አበባዎችን፣ ወዘተ በምሳሌነት ተጠቅሟል። እነዚህ ሁሉ ከማየትና ከማስተዋል የተገኙ ምሳሌዎች ናቸው። እኛም ከምናየው ነገር ሁሉ ምሳሌዎች ማውጣት እንችላለን።

ለ) ጋዜጣ (News Paper)


© 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas

ሐ) ታሪክ (History)

መ) ሥነጽሑፍ (Literature)

ሠ) የሰዎች የሕይወት ታሪክ (Biography)

ረ) ሳይንስ፣ ሥዕል፣ አዲዲስ ግኝቶች

ሰ) እንስሳና አራዊት፣ አዕዋፍ፣ ማዕድን-- ጌታ ስለ ቀበሮ፣ ስለ ተኩላ፤ ስለ ግመል፣ ስላ አዕዋፍ፣ ስለ በግ፣ ስለ ፍየል....ወዘተ ሁሉ ተናግሮአል።

ሸ) ልጆች

ቀ) የምሳሌ መጽሐፎች

በ) ንፁህ ፈጠራ (Imagination)፥ ንፁህ ፈጠራ ፈጥሮ ያንን ለምሳሌነት ለመጠቀም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል። ንፁህ ፈጠራ መጠቀም ማለት ውሸት መዋሸት ማለት እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ሊሆን ይገባል። የሚፈጠሩት ፈጠራዎች ሁሉ በጥንቃቄ የተፈጠሩና በእውነት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይገባል። ምሳሌ፥ 2 መሶብ ይዘው ከሰማይ ወረዱ። እነዚህም የምስጋናና የልመና መቀበያ መሶቦች ነበሩ። የሚሉት ምሳሌዎች ከእውነት ለአልራቁ ንፁህ ፈጠራዎች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

የመናኝ ጉዞ የተሰኘው መጽሀፍም ፈጠራ ነው። እነዚህን የመሳሰሉ ምሳሌዎች በፈለግን ጊዜ ለማግኘት እንድንችል የምሳሌዎች ባንክ ማስቀመጥ መልካም ሃሳብ ነው።

ምሳሌዎችን ሲጠቀሙ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

ሀ) በራስ ልምምድ ላይ ያተኰሩና ያንን ልምምድ የሚያደንቁ ምሳሌዎችን ማብዛት መልካም አይደለም።

ለ) በየጊዜው አዳዲስ ምሳሌዎችን መጠቀም መልካም ነው።

ሐ) ምሳሌ የምንጠቀመው ለስብከታችን ብርሃን እንዲሰጥ ብቻ ነው። ስለዚህ የስብከታችን ብርታትና ጥንካሬ ያለው ምሳሌዎቹ ላይ ስላልሆነ ስብከታችን በምሳሌ መጥለቅለቅ አያስፈልገውም።

መ) የምናቀርበው ምሳሌ ከስብከታችን ርዕስ ውጭ መሆን አይኖርበትም።

ሠ) ምሳሌዎችን ስናቀርብ በነገሩ እንደሰለጠነበትና እንደሚያቀው ሰው መሰለህ ማቅረብ የለብንም። እንደዚህ ብናደርግ መሣሣት እንችላለን። ምሳሌአችን ከባዮሎጂ ቢሆን እንደተራቀቀ ባዮሎጂስት የማናውቀውን ለማብራራት መሞከር ተገቢ አይደለም።

ረ) ምሳሌህ አሳፋሪና ተገቢ ያልሆነ እንዳይሆን ጥንቃቄ አድርግ። በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1962 ላይ አንድ ጓደኛችን የሚሰብከው ምሳሌ በጣም ለመቀበል ያስቸግረኝ ነበር። ስለጌታ ጓደኝነትና ጥበቃ ለመስበክ ስለውሻ ይናገርና "ጌታ ለእኛ ልክ እንደዚህ ውሻ ነው።" ይል ነበር። ይህ ፀያፍ የምሳሌ አቀራረብ ነው።

አንድ ሌላ ሰው በአዝዚህ ዘመናት ከትምህርት ቤቱ የውሃ መዋኛ ውስጥ ሆኖ ወደ ክፍል እንዲገቡ ደውል ስለተደወለ መፀዳጃ ክፍል ለመሄድ ጊዜ ስለልነበረው እዚያው ውሃ ውስጥ ማንም እንዳያየው ሶቶ በመግባት ያደረገው ነገር እንደነበረና ስለገጠመው ችግር በማብራራት ትያትራዊ በሆነ አቀራረብ ምሳሌ ያቀርብ ነበር።

ሌላ ሰው ደግሞ ሴተኛ አዳሪ እንዴት ሰው እንደምታጠምድ ሥዕላዊ አድርጐ ያቀርብና ቤተክርስቲያን ሰዎችን እንደዚያ ማጥመድና መጥራት እንዳለባት ለማብራራት ይሞክር ነበር። በመሰረቱ አመንዝራ ሴት ለቤተክርስቲያን መሳሌ ሆና መቅረብ አትችልም። ስለዚህ ምሳሌ ስንሰጥ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።

## የስብከት አዘጋጃጀት

ስብከት ማዘጋጀት ጊዜ የሚጠይቅና ብዙ መሥራት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። እሁድ ጥዋት ለመስበክ ያለቅድመ ዝግጅት እሁድ ጥዋት ስብከት ፍለጋ መንጐዳጐድ ጥሩ አይደለም።

ስብከትን ለማዘጋጀት የሚፈጀው ጊዜ የሚያጠቃልለው፥

ሀ) በየዕለቱ ቃሉን ያነበብንበትንና ያጠናንበትን ጊዜ ሁሉ።

ለ) ለስብከታችን የሚረዱ ማቴሪያሎች የፈለግንበትንና የሰበሰብንበትን ጊዜ ሁሉ።

ሐ) በፀሎት በጌታ ፊት ያጠፋነውን ጊዜ ሁሉ።

መ) ሃሳባችንን ሰብስበን ጊዜ ወስደን የስብከታችንን ርዕስና አስተዋጽኦ (out-line) ያወጣንበትን ጊዜ ሁሉ። ቀጥሎም ሀሳባችንን አርመንና አስተካክለን የምንሰብከውን በስብከት ደብተራችን የጻፍንበትን ጊዜ ሁሉ ነው። ስለዚህ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ይጠይቃል። ስብከት ጊዜ ተወስዶ መዘጋጀት ያለበት ነገር ነው። አንዳንድ ሰዎች "አፍህን ክፈት እሞላዋለሁ።" ተብሏል የሚል ቃል እየጠቀሱ ያለምንም ዝግጅት በመድረክ ላይ ይወጣሉ። መድረክ ላይ ከመውጣት በፊት ለስብከቱ ዝግጅት፤ ቀደም ብሎም ገና ስብከት ሳይሰጠን በግል ያለተማርነውና ያላጠናነው ወደ ሕይወታችን ያልገባ ቃል ስለማይወጣ መድረክ ወጥተን አፋችንን ብንከፍት ዝም ብሎ አፍ መከፈት ብቻ ይሆናል።

ስብከት ማዘጋጀት ልክ ምግብን እንደማዘጋጀት ነው። ሁሉ ነገር በጥንቃቄ መቀመም፣ መደባለቅና በስሎ ለተመጋቢ መቅረብ አለበት። ደግሞም አንድ ጊዜ ብቻ ምግብ ተሰርቶ ለብዙ ቀን ስለማይበላ በየጊዜው አዲስ (fresh) ምግብ ተሰርቶ መቅረብ አለበት። ስለሆነም ሰባኪ ይህንን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ ለጌታው የግብር ይውጣ የመሰለ አገልግሎት ሳይሆን በበኩሉ የሚችለውን የመጨረሻ ድካሙን ሊያቀርብ ያስፈልጋል።

## የስብከት ዝግጅት እነኝህን ሁለት ነገሮች ያካትታል

ሀ) አጠቃላይ ዝግጅት፥ ሰባኪ የማያቋርጥ የግል ጥናት ያስፈልገዋል። መጽሐፍ ቅዱሱን ማጥናት ያለበት ስብከት ለመስበክ ብቻ መሆን የለበትም በየጊዜው መማር፣

ማወቅ፣ ማደግ አለበት። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለማወቅና ለማጥናት የሚረዳን ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ቃሉን ማወቅ አለብን። ለመስበክ ተብሎ ሳይሆን በግል ሕይወት ለማደግ ሲባል ቃሉ በየጊዜው መጠናት አለበት።

ለ) ልዩ ዝግጅት፥ ልዩ ዝግጅት የምንለው የምንሰብክ መሆናችን ከተነገረንና ካወቅን በኋላ ያለው ጊዜ ነው። በእነዚህ ቀናትና ሰዓታት ውስጥ ማድረግ የሚገባን፥

- በፀሎት በጌታ ፊት ጊዜ ማጥፋትና መንፈስ ቅዱስ የምንሰብከውን መልእክት ከቃሉ እንዲሰጠን መጠየቅ።
- መንፈስ ቅዱስ ልባችን ውስጥ ላስቀመጠው ሃሳብ ጥቅስና ርዕስ መፈለግ።
- ጥቅሱ በተለያዩ ትርጉሞችና ቢቻልም በግሪክና በዕብራይስጥ ያለውን ትርጉም ሁሉ መመልከት። ጥቅሱን ማጥናት፣ ማስታወሻ መያዝ። ጥቅሱንና (Context) መርምሮ ማወቅ።

ሐ) የሊቃውንት አስተያየት መጻሕፍት (Commentary) ወዘተ መመልከትና ሃሳቡን ማጥናት።

መ) መልዕክቱን በራስ ሕይወትና ልምምድ መፈተን። ብዙ ጊዜ ሕይወታችንን የነካ ሃሳብ ከልባችን ስለሚፈልቅ የሌሎችንም ልብ ይነካል። በራሱ ሕይወት ከፈተነውና ከተለማማደው በላይ የሚሰብክ ሰባኪ በሙሉ ስሜትና ተመስጦ (Conviction) መስበክ አይችልም።

ሠ) ስብከትን ማዘጋጀት።

ረ) መስበክ።

## የሚሰበክላቸውን ሰዎች ማንነት ማወቅ

ስብከት ሲዘጋጅ ለእነማን እንደሚዘጋጅ ማወቅ ይገባል። ምክንያቱም የመልእክቱ ተቀባዮች የተለያዩ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ሀ) የልጆች ስብከት፥ ለልጆች የምናዘጋጀው ስብከትና አቀራረቡም ካዋቂዎች ይለያል። ቋንቋው፣ ምሳሌው ሁሉ በልጆቹ የአእምሮ ደረጃ መሆን አለበት።

ለ) ለአዋቂዎች

ሐ) የተማሩ፥ እነዚህ አእምሮአቸው ያለበት ደረጃ የሚደርስ መልእክት ይፈልጋሉ። ከአእምሮአቸው በታች ለአለመስበክ የሚቻለንን ጥንቃቄ ማድረግ።

መ) ያልተማሩ፥ ላልተማሩ አድማጮች በሚገባ መንገድ መቀረብ አለበት።

ሠ) `የለቅሶ ስብከት፥ ለቅሶ ከሆነም ስብከቱ ሀዘንተኞቹን አጽናንቶ ለቀሩት የወንጌልን ምስራች የሚያበስር መሆን አለበት። ሟቹ ክርስቲያን ከሆናና ካልሆነ እንኳን ያሰባበካችን መንገድ ይለወጣል። ለምሳሌ ሟቹ የማያምን ከሆነ ስለ ወደፊቱ ተስፋው መናገር አግባብ የለውም። ያ ከሆነ የሟቹን ሕይወት የሚያውቁ ሰዎች እንደርሱ ባያምኑ መጨረሻቸው መልካም ሊመስላቸው ይችላል።

ረ) የሠርግ ስብከት፥

ከዚህም ሌላ ለመንፈሳዊ መነቃቃት (revival) ለዶክትሪን ትምህርት፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ... ወዘተ ሁሉ ዝግጅታችን የተለያየ ይሆናል።

## የስብከት አቀራረብ

ጥሩ ስብከት ተዘጋጅቶ አቀራረቡ ጥሩ ካልሆነ አይጠቅምም። ስለዚህ አቀራረብን በተመለከተ ጥንቃቄ ልንወስድባቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ። እነርሱም፥

ሀ) አለባበስን በሚመለከት፥

አለባበስ ተገቢ ካልሆነ ሰዎች መልእክቱን ማዳመጥ አይችሉም። ስለዚህ ተገቢ የሆነ የልብስ አለባበስ ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ ወንዶች ሊወስዱት የሚገባ ልዩ ጥንቃቄ (ለምሳሌ የሱሪው ዚፕ መቆለፋን ርግጠኛ መሆን፣ አይነታቸው ያልተለያየ ካልሲ ላለመልበስ መጠንቀቅ፣ ቁልፋ ያልተበጠሰ ሸሚዝ መልበስና ሌሎችም ያድማጮችን ልብ ከተናጋሪ ሊለዩ በሚችሉ ነገሮች ላኢ ትንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ሴት ሰባኪዎች ደግሞ ሊጠነቀቁበት ከሚገባቸው ነገሮች መካከል፥ ከመጠን ያለፈ አጭር ቀሚስ፣ በሰውነት ላይ የተጣበቀና ሰውነትን የሚያስነብብ ልብስና የመሳሰሉት የአድማጮችን ልብ ሊሰልቡ ስለሚችሉ፥ አስፈላጊው ጥንቃቄ መጉደል የለበትም።

ለ) የድምፅ አጠቃቀም

ሐ) የድምፅ ማጉያ አጠቃቀም

መ) የስብከቱ ርዝመት የተመጠነ መሆን አለበት። እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1959 ዓ.ም በናዝሬት ከተማ በአንድ ቀን ለ10 ሰዓት ያህል የተሰበከ ስብከት ነበር)።

ሠ) አይናችን ሰዎች ላይ ማረፍ ይኖርበታል። ጣራ ጣራ ወይም ምድር ምድር መመልከትና ዓይንን፣መጨፈን ካድማጮች ያራርቃል። አይናችን አድማጮች ላይ ሲሆን ስብከታችንን ያደምጡ ወይም አያደምጡ እንደሆነ ማየት እንችላለን። መሰላቸታቸውንም ለመረዳት ይጠቅማል። ደግሞም የአይን ግኑኝነት እያደረገን ስንሰብክ አድማጩ ለእኔ ነው የሚነገረው ብሎ ስለሚያስብ ነቅቶ ያዳምጣል። ማንቀላፋትም አይችልም።

ረ) የአቀራረብ ዘዴ (style)

- በክርክር መልክ
- በጥያቄ መልክ
- በማነፃር (comparisons)
- በማወዳደር (contrast) መልክ ስብከት ማቅረብ ይቻላል።

ስለዚህ ለስብከታችን አቀራረብ የዝግጅታችንን ያህል ጥንቃቄና ማስተዋል ልንጨምርበት ይገባል።

## ምክር

ሀ) ወደ መድረክ ስንወጣ ለመናገር ያህል ሳይሆን አንድ ጊዜ ለቅዱሳን ስለተሰጠው እምነት (የወንጌል ቃል) ለመጋደልና የምሥራቹን ለማብሰር ነው። ስለዚህ ስብከት ዓላማው ምን እንደሆነ አንርሳ።

 © 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas 

ለ) የምንናገረው ነገር በመጀመሪያ በራሳችን ሕይወት ክብደት ይኑረው። በእኛ ሕይወት ክብደት ካለው ለሌላውም ትርጉም ይሰጣል። በእኛ ህይወት ክብደት የሌለው ነገር ለሌላውም አይጠቅምም።

ሐ) ስብከት የንግግር ችሎታ ሳይሆን ሕይወት ነው። የምንሰብከውና ሕይወታችን የሚቃረን ከሆነ ማንም የሚሰማን የለም።

መ) ለራሳችን ታማኝ እንሁን። ስንሰብክ ሌላን ሰባኪ መኰረጅና እርሱን ለመምሰል አንሞክር ራሳችንን እንሁን።

ሠ) ተስሚ እንሁን። ቃላት መደጋገምና መሙያዎችን ማብዛት አድማጭን ያሰለቻል።

ረ) የመድረክ አገልግሎታችን በፀሎት የተደገፈ ይሁን። ብዙ ሰዎች መፀለይ ሲከብዳቸው መስበክ ግን ይቀላቸዋል። ነገር ግን በመድረክ ላይ የምናገኘው ኃይል በፀሎት የምናጠፋው ጊዜ ውጤት ነው። ስለዚህ በፀሎት ያልተደገፈ አገልግሎት ከመስተት መቆጠብ ይደገፋል። ፆምና ፀሎትም የሕይወታችን ልምምድ ይሁን። ይህ ለመድረክ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለክርስትና ሕይወት ዲሲፕሊንም አስፈላጊ ነው። ሁልጊዜ የመፀለይና የመጾም ልምምድ ካለን፥ መልእክት መቀበልም ሆነ ማቅረብ ተራራ እንደመውጣት አይሆንብህም።

ሰ) ስንሰብክ በማን ፊት እንደምንቆም አንርሳ። ስንሰብክ በሰዎች ፊት ብቻ ሳይሆን፣ በምትሰብከው ጌታ ፊት መቆማችንን መርሳት የለብንም። ስለዚህ አይናችን በእግዚአብሔር ላይ ይሁን። አገልግሎታችንን ባክብሮትና በፍርሀት እናድርገው። የልማድና የድፍረትን ነገር መተው አስፈላጊ ነው።

ሸ) ስብከት የቃላት አሰካክን ማሳመር አይደለም። በእንግሊዝ አገር አንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ዶክተር ዮሴፍ ፓርከር (Dr. Joseph Pareker) ይባሉ የነበሩትን ሰው ስብከት ስመተው ሲወጡ እርስ በእርሳቸው "አቤት የንግግር ችሎታ! አቤት የቃላት አመራረጥ! ሲናገሩ ያፈዙ የለም እንዴ!" ተባባሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች በሚቀጥለው እሁድ በአንድ ላይ ስፐርጀን (Spurgeon) ከሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያን ሄደው የሳቸውን መልእክት ሰሙ። ከዚያ ሲወጡ በመካከላቸው ትልቅ ፀጥታ ሆነ። ቆይቶ አንዱ ለሌላው "ምን ዓይነት ክርስቶስ!" (what a Christ) ተባባሉ። ምክንያቱም ስፐርጀን ያሳዩአቸው ክርስቶስን ስለነበር ነው።

ከቃላት እሩምታ በቀር ተጨባጭ ፍሬ ነገር ከመድረኩ አገልግሎት ያላገኘው ሌላው ደግሞ ስለሰመው ስብከት ሲገልጽ "ታላቅ ነፋስ፤ ከባድ መብረቅና የነጐድጓድ ድምፅ፥ ነገር ግን ዝናብ የለም" ሲል ተናግሮአል። ኪዚህ የምንረዳው የቃላት አመራረጥን ማወቅና ሰዋሰው መልካም ነገር ቢሆንም ስብከት ማለት እንዳልሆነ ነው። ስለዚህ ስንሰብክ ለሰዎች የሚቀርላቸው ነገር መስጠት እንዳለብን ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነው።

ቀ) ለተሰበከው እውነት ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልግም። የተሰበከው ከቃሉ የወጣ እውነት ካልሆነ፣ ወይም የሰብከቱ መንፈስ ትክክል ካልሆነ ይቅርታ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እውነት "የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል።" በማለት የሚሰብክ ሰባኪ ሰዎች ስብከቱን በተቃወሙ ቁጥር ንሰሀ መግባት አይገባውም። አንድ የጥርስ ሐኪም (Dentist) ጥሩሱን ታሞ ከሚሰቃየው ሰው ለሚሰማው ስቃይ (pain) ምክንያት የሆነውን የበሰበሰ ጥርስ በማውጣቱ በሽተኛውን "አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርግልኝ።" አይለውም። አንድ ሰባኪም እግዚአብሔር የሰጠውን መልእክት ማቅረብ እንጂ ስብከቱ በሁሉ ዘንድ የተወደደ እንዲሆን ለማድረግ አይገደድም።

በ) ነቀፌታን ጠብቅ። የምንሰብከውን ስብከት ስምተው ሁሉ ሊደሰቱ አይችሉም። በተለይም የማይለወጠውን እውነትና የጽድቅ ነገር ነብከን ቅር የሚለው ሰው ከጉባዔው ውስጥ አይጠፋም። ከክርስቶስ ስብከት ጀምሮ ዛሬ እስካሉት አገልጋዮች ስብከት ሁሉንም ሰው የሚያስደስት ስብከት ተሰብኰ አያውቅም። እንኳን በመልእክቱ ይዘት ቀርቶ በቃላት አሰካክና የንግግር ችሎታችን ሊነቅፉን የሚፈልጉ አይታጡም። ዲ.ኤል . ሙዲ (D.L. Moody) የተባሉ ሰው አንድ ጊዜ ሰብከው ከመድረክ ሲወርዱ አንድ ሰው "በዛሬው ስብከትህ 8 ዓይነት የሰዋሰው (grammar) ስህተት አድርገሃል፤" ሲል ነቀፋቸው። እሳቸውም "ወዳጄ ሆይ! እኔ ብዙ ትምህርት የለኝም። ወላጆቼም አላስተማሩኝም። የተሻለ ትምህርት ቢኖረኝ ኖሮ ደስ ባለኝ። ነገር ግን ይህችኑ ያለችኝን ትንሽ እውቀትና ሰዋሰው ለጌታዬ ክብር አውላታለሁ። አንተስ?" ሲሉ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት። እግዚአብሔር ከችሎታችን ይልቅ የሚፈልገው እሺ ብለን ለማገልገል መፍቀዳችንን ነው።

ተ) የምንሰብክበት ዓላማ ከመጥምቁ ዮሐንስ ዓለማ ጋር ይስማማ። መጥምቁ ዮሐንስ በዮሐንስ ወንጌል 3፥ 31 ላይ እንደምናነበው ዓላማው ክርስቶስ ከፍ እንዲል እሱ ግን ዝቅ እንዲል ነበር። አኛም ለግል ዝና፣ ለክብር፣ ለጥቅምና ለማንኛውም ያልተቀደሰ ዓላማ መስበክ የለብንም። የምንሰብክበትና የምናገለግልበት ዓላማ ከዮሐንስ ወንጌል 3፥ 31 ጋር ካልተስማማ ስብከቱን ትተን ሕይወታችንን ለማስተካከል ከመስቀሉ ሥር እንውደቅ።

## ተፈጸመ


© 2007 | የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት ቤተክርስቲያን | Houston, Texas